29ኛ ዓመት ቁጥር 28
29th Year, No. 28

ባሕር ዳር ግንቦት 4 ቀን 2017 ዓ.ም
Bahir Dar, May 12, 2025

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 4666.70 ብር
Unit Price Birr 4666.70

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፫/፪ሺ፲፯ ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ

Content

Proclamation No. 293/2025
The Amhara National Regional State Advocacy Service Licensing and Administration Proclamation

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፫/፪ሺ፲፯ ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደርን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የሕዝብ ጥቅምን በማስጠበቅና ፍትሕን በማስፈን ዙርያ የተደራጀ የመንግሥትና የሙያተኞችን ተዋጽኦ ያማከለ የጋራ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቀጣይነትና ድርጅታዊ ዋስትና ያለው የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የጥብቅና ድርጅት የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በክልሉ ውስጥ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥና የፍትሕ ሥርዓቱን መሠረታዊ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ጠበቆች እና የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No. 293/2025
A Proclamation Issued to Provide Advocacy Service Licensing and Administration In The Amhara National Regional State

WHERE AS, it is necessary to provide professionally independent advocacy service by establishing a joint administration system that balances respective roles of the government and practitioners in safeguarding the public interest and ensuring justice;

WHERE AS, it is necessary to lay down a system that directs and governs law firms which provide sustainable and institutionally guaranteed advocacy service to users of advocacy service;

WHERE AS, it has become necessary to provide a system which advocates and law firms are guided to ensure the rule of law and meet objectives of the justice system in the region;

ለዚሁ ያመች ዘንድ በሥራ ላይ ያለውን የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆች ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፩ሺ፱፻፺፬ ዓ.ም (እንደተሻሻለ) ክልሉ ከሚገኝበት የእድገት ደረጃና ከአዳጊ ፍላጎቶች ጋር አጣጥሞ በማሻሻል ጠበቆች እና የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶች በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን አስተዋጽኦ በዓይነትም ሆነ በመጠን ከፍ ማድረግና የኅብረተ-ሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ (፩) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ክልል የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፫/፪ሺ፲፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ቢሮ" "መምሪያ"** እና **"ጽሕፈት ቤት"** ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ፣ ፍትሕ መምሪያና ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

፪/ **"የቢሮ ኃላፊ" "የመምሪያ ኃላፊ"** እና **"የጽሕፈት ቤት ኃላፊ"** ማለት እንደቅደም-ተከተላቸው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ፣ ፍትሕ መምሪያና ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ነው፡፡

Where as, it is needed to increase the contribution of advocates and law service firms in the justice system in kind as well as amount and therby to ensure greater benefit of the society by revising the Amhara National Regional State Advocacy Service Licensing, Registration and Controlling Code of Conduct of Advocates Proclamation No. 75/2002 (as amended) in relation to the development level and increasing demand of the region;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with the powers vested in it under Article 49, Sub-article 3 /1/ of the revised Constitution of the National Region, here by issued this proclamation.

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as *"***The Amhara Region Advocacy Service Licensing and Administration Proclamation No. 293/2025***."*

2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ **"Bureau" "Department"** and **"Office"** means the Amhara National Regional State Justice Bureau, Justice Department and Justice Office respectively.

2/ **"Head of the Bureau" "Department Head" and "Office Head"** means Head of the Amhara National Regional State Justice Bureau, Justice Department and Justice Office respectively.

፫/ **"ጠበቃ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ፍቃድ የተሰጠዉ ሰዉ ነዉ፡፡

፬/ **"የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ"** ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን መስፈርቶች ላሟላ ሰው የክልሉ ሥልጣን በሆኑ ጉዳዮች ላይ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት የተሰጠው የምስክር ወረቀት ነው፡፡

፭/ **"የታክስ ክሊራንስ"** ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሰው ላገኘው ገቢ ግብር ስለመክፈሉ ከግብር ሰብሳቢው አካል የሚሰጥ ማስረጃ ነው፡፡

፮/ **"የጥብቅና አገልግሎት"** ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም የሕግ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) በሕግ ጉዳዮች ላይ ምክር መስጠት፣ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ወይም የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን ጨምሮ የማደራደር ሥራ መሥራት፤

ለ) የሕግ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም ለማናቸውም አካል በደንበኛው ስም ሰነድን ማቅረብ ወይም ጉዳይን ማስፈጸም፤

ሐ) በፍርድ ቤቶች፣ አስተዳደራዊ ጉባዔዎች፣ ከፊል የዳኝነት ሥልጣን ባላቸዉ አካላት፣ በግልግል ዳኝነት ጉባዔዎች እና በሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ መድረኮች ደንበኛን ወክሎ መቅረብ እና መከራከር፡፡

፯/ **"ማኅበር"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የክልሉ ጠበቆች ማኅበር ነው፡፡

3/ **"Advocate"** means a person licensed to provide advocacy service pursuant to this Proclamation.

4/ **"Advocacy License"** means a license granted for a person who fulfills the requirements specified under this Proclamation to provide advocacy professional service in the regional jurisdiction.

5/ **"Tax Clearance"** means a certificate given to the advocate, as an evidence of paying income tax, by a tax collecting authority to advocacy license holder.

6/ **"Advocacy Service"** means any kind of legal service provided by an advocate or law firm with payment of fee or in expectation of direct or indirect future benefit, or pro bono, including the following:

A) Providing consultation on legal issues, conducting negotiations including criminal transgression of laws submitted in private petition;

B) Drafting legal documents or submitting documents on behalf of a client or executing a case;

C) Representing a client and litigating before courts, administrative tribunal, quasi-judicial institutions, arbitral judicial tribunals and other alternative dispute resolution forums.

7/ **"Association"** means the Regional Bar Association established pursuant to this Proclamation.

፰/ **"የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ"** ማለት የራሱ የሆነ የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖረው በሌላ ጠበቃ አመራር ሥር በመሆን የሕግ አስተያየት ከመስጠት ጀምሮ የሕግ ነክ ሰነዶችን በማዘጋጀት ጠበቃውን የሚያግዝ በሕግ ትምህርት ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው ሰው ነው፡፡

፱/ **"የጠበቃ ረዳት"** ማለት በጠበቃ የተዘጋጀ የክስ ማመልከቻና መከላከያ መልስን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፋይል የሚያስከፍት፤ የፍርድ ቤት መጥሪያ፣ ትዕዛዝ እና የዉሳኔ ግልባጭ የሚያወጣ እና ለሚመለከተው ሰው የሚያደርስ ሰው ነው፡፡

፲/ **"አገናኝ"** ማለት የጥብቅና አገልግሎትን በሚመለከት ጠበቃን ወይም የጥብቅና ድርጅትን እና ባለጉዳይን በማገናኘት ከአንዱ ወይም ከሁለቱም ወገን ክፍያ ወይም ኮሚሽን በመቀበል ወይም ወደፊት ለመቀበል በማሰብ ከጥብቅና ሥነ-ምግባር ውጪ ባለጉዳዩን በማግባባትና በማሳመን ባለጉዳዩ እርሱ የመረጠለትን ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንዲይዝ የሚያደርግ ወይም የሚያግባባ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

፲፩/ **"በአገናኝ አማካኝነት መሥራት"** ማለት በፍርድ ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሌሎች የፍትሕ ተቋማት ወይም በማንኛውም ስፍራ አገናኞችን በማሠማራት ወይም በተሠማሩ አገናኞች ወይም ከየፍትሕ ተቋማቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር ከጥብቅና ሥነ-ምግባር ውጪ የጥብቅና ወይም የሕግ አቤቱታ ፀሐፊ አገልግሎት ፈላጊዎች ወደ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ወይም የሕግ አቤቱታ ፀሐፊው እንዲመጡ የማድረግ ተግባር ነው፡፡

፲፪/ **"ነፃ የጥብቅና አገልግሎት"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ለተዘረዘሩት የጥብቅና አገልግሎት ፈላጊዎች ያለምንም ክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ የጥብቅና አገልግሎት ነው፡፡

8) **"Law-Clerk"** means a person who holds at least a diploma in law but do not have an advocacy license and helps the advocate, being under direct supervision of the later, in preparing law-related documents starting from providing legal opinions.

9/ **"Advocate's Assistant"** means a person who opens files by submitting charge petition and defending response, prepared by an advocate, to a court; receives summons, orders and copies of judgements from courts and delivers it to the concerned persons.

10/ **"Intermediary"** means any person who introduces a potential client seeking advocacy services or otherwise persuades him, out of advocacy discipline, to engage the services of an advocate or law firm of his choice, in consideration of immediate or future payment or commission from one or both parties.

11/ **"Working through an Intermediary"** means a practice by which an advocate or law firm engages intermediaries or already engaged intermediaries in courts, prisons, police stations, other justice institutions or at any place to make advocacy or legal secretary service seekers come to an advocate or law firm or to law clerk out of advocacy discipline by establishing relationships with each justice institution heads or employees in a sense of mutual personal enrichment.

12/ **"Pro Bono Advocacy Service"** means an advocacy service provided by an advocate or law firm with no charge to persons listed under this Proclamation as in need of such services.

፲፫/ **"ደንበኛ"** ማለት ስለራሱ ወይም ስለሌላ ሰው ጉዳይ ማንኛውንም የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት ከጠበቃ ወይም ከጥብቅና ድርጅት ጋር የተዋዋለ ወይም የጉዳዩን ፍሬ ነገር ያስረዳ ሰው ነው፡፡

፲፬/ **"የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት"** ማለት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የጸና የጥብቅና ፍቃድ ያላቸዉ ጠበቆች የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚያቋቁሙት ድርጅት ነው፡፡

፲፭/ **"አባል"** ማለት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ አባል የሆነ ጠበቃ ነው፡፡

፲፮/ **"መዝገብ"** ማለት ጠበቆች እና የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶች የሚመዘገቡበት በቢሮው የሚጠበቅ ሰነድ ወይም የሕግ አቤቱታ ፀሐፊዎች የሚመዘገቡበትና በዞን ወይም ብሔረሰብ አስተዳደር ፍትሕ መምሪያ የሚጠበቅ ሰነድ ነው፡፡

፲፯/ **"አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ"** ማለት በክልሉ ፍርድ ቤቶች እና በሌሎች የዳኝነት አካላት የስረ-ነገር ሥልጣን ስር በሚወድቁ የክልል ጉዳዮች ላይ ለመከራከር እና ሌሎች የጥብቅና አገልግሎቶችን ለመሥጠት የሚያስችል ፈቃድ ነው፡፡

፲፰/ **"ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ"** ማለት በክልሉ በሚገኙ ወረዳ ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ሥልጣን ስር በሚወድቁ የክልል ጉዳዮች ላይ ለመከራከር እና ሌሎች የጥብቅና አገልግሎቶችን ለመሥጠት የሚያስችል ፍቃድ ነው፡፡

፲፱/ **"ልዩ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ"** ማለት ጉዳያቸውን በራሳቸው ይዘው መከራከር የማይችሉ ሰዎችን መብትና ጥቅም ለማስከበር ሲባል ማናቸውንም ዓይነት የሕግ አገልግሎት ያለምንም ክፍያ በነፃ ለመስጠት ፍላጎቱ ላላቸው ጠበቆች፣ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶች፣ የብዙኃን ማኅበራት፣ የሙያ ማኅበራት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማዕከላትና መሰል ዓላማዎችን ለማራመድ ለተቋቋመ አካል በቢሮው የሚሰጥ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ነው፡፡

13/ **"Client"** means a person who enters into contracts with an advocate or law firm to obtain advocacy services for him or for a third party or who tells facts of the case to an advocate.

14/ **"Law Firm"** means an organization established to provide advocacy service by two or more licensed advocates.

15/ **"Partner"** means a licensed advocate who is a member of a law firm.

16/ **"Register"** means a record which is registered by advocates and law firms and kept by the bureau or registered by law clerks and kept by zonal or nationality administration justice departments.

17/ **"First Level Advocacy License"** means an advocacy license which enables an advocate to render advocacy services of regional cases fall under the jurisdiction of regional courts and other judicial bodies.

18/ **"Second Level Advocacy License"** means an advocacy license which enables an advocate to render litigation and other advocacy services of regional cases fall under the jurisdiction of wereda courts found in the region.

19/ **"Special Advocacy License"** means an advocacy license given by the bureau to advocates, law firms, public associations, professional associations, higher educational institutions, free legal aid service centers and entities established to promote similar objectives that are interested in providing any type of legal service free of charge in order to protect the rights and interests of people who are unable to defend their own cases.

፳/ "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ነው፡፡

፳፩/ "ዋና ጉባዔ" ወይም "ንዑስ ጉባዔ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በክልል ወይም በዞን ደረጃ የጠበቆችንና የጥብቅና ድርጅቶችን የዲሲፕሊን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

፳፪/ "ሥልጠና" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በማኅበሩ ወይም ማኅበሩ እውቅና በሰጠው ተቋም አማካኝነት ለጠበቆች በሥራ ላይ እያሉ የሚሰጥ የሕግ ሥልጠና ነው፡፡

፳፫/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በፍትሐብሔር ሕጉ የተሰጠዉ ትርጉም ይኖረዋል፡፡

፳፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፳፭/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ከቢሮው የጥብቅና ፈቃድ በወሰደ ጠበቃ፣ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት እና ልዩ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ባለው ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባ እና እድሳት

ንዑስ ክፍል አንድ

ስለ ፈቃድ አሰጣጥ

፬. የጥብቅና ፈቃድ መርሆዎች

፩/ ማንኛዉም ሰዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

፪/ የጥብቅና ፈቃድ ቋሚ ሥራ ላለው ሰው አይሰጥም፤

፫/ ማንኛዉም የጥብቅና ፈቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰዉ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፤

20/ **"Board"** means the Advocates' Administration Board established under this Proclamation.

21/ **"Main Council"** and **"Sub council"** means a body which examines and gives dicision of disciplinary matters of advocates and law firms at regional and zonal levels respectively.

22/ **"Training"** means legal on job training offered to advocates by the Association or an Institution accredited by the Association to offer such trainings based on this proclamation.

23/ **"Force Majeure"** shall have the definition given under the Civil Code.

24/ **"Person"** means natural or juridical person.

25/ In this Proclamation any expression in the masculine gender includes the feminine gender.

3. Scope of Applications

This Proclamation shall be applicable on advocates, law firms an d on persons who are granted special advocacy license by the bureau in accordance with this Proclamation.

PART TWO

LICENSING, REGISTRATION AND RENEWAL

SUB-PART TWO

LICENSING

4. Principles of Advocacy License

1/ No person shall provide advocacy services without having a license;

2/ Advocacy license shall not be given to a person having permanent job;

3/ A person who applies to obtain an advocacy license shall fulfill the requirements provided in this Proclamation;

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰዉ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በዘር ወይም በማኅበራዊ አመጣጡ፣ በፖለቲካ አመለካከቱ፣ በንብረቱ፣ በትዉልዱ፣ በአካል ጉዳቱ ወይም ማንኛዉንም ተመሳሳይ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ፈቃድ አይከለከልም።

፭. ፈቃድ የማያስፈልግበት ሁኔታ

የሚከተሉት አካላት የጥብቅና ፈቃድ ሳያስፈልጋቸዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡-

፩/ ስለራሱ ጉዳይ የሚከራከር ሰዉ፤

፪/ ያለክፍያ ለትዳር ጓደኛዉ፣ ለወላጁ፣ ለልጁ፣ ለአያቱ፣ ለእህቱ፣ ለወንድሙ፣ ለትዳር ጓደኛዉ ወላጆች፣ ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰዉ የሚከራከር ሰዉ፤

፫/ ከሥራዉ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚከራከር ዐቃቤ-ሕግ፤

፬/ ሕጋዊ ሰውነት ባለው የንግድ ድርጅት፣ የሲቪል ማኅበረ-ሰብ ድርጅት፣ ሕዝባዊ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማኅበር ወይም በሌላ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሠረት በተቋቋመ ድርጅት ተቀጥሮ የተወከለ ሰው፤

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛዉም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ኃላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰዉ፤ ወይም

፮/ ማንኛውም የሠራተኛ ማኅበር መሪ ወይም ማኅበሩ የሚወክለዉ ሰዉ፤

፯/ የቡድን ጥቅምን ይዞ የሚከራከር ማንኛውም ሰው።

፮. የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች

የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች፡-

፩/ አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ፤

፪/ ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድና፤

፫/ ልዩ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ናቸው።

4/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, no person shall be denied a license on grounds of gender, religion, language, ethnic or social background, political outlook, economical status, origin, physical disability or other similar conditions.

5. Condition of License Unnecessity

The following bodies may provide advocacy services without the need for an advocacy license:

1/ Any person litigating on his own case;

2/ A person who litigates for, without charge, his spouse, parent, child, grand parent, sister, brother, parent of his spouse, a person to whom he is designated tutor or guardian;

3/ A Public prosecutor on cases related to his job;

4/ A person employed and assigned by a business organization having legal personality, civil society organization, public organization, religious institution, professional association or organization established in accordance with relevant law;

5) An official or head of public enterprise or a person represented by him who litigates on behalf of public office or public enterprise;

6/ Any leader or representative of labor union; or

7/ Any person litigating for group interests.

6. Types of Advocacy Licenses

Types of advocacy licenses:

1/ First-Level Advocacy License;

2/ Second-Level Advocacy License; and

3/ Special Advocacy License.

፯. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለዉ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

ለ) ዕዉቅና ከተሰጠዉ የሕግ ትምህርት ቤት ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቀ፤

ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሠራበት ከነበረበት ተቋም ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ዉስጥ በዲሲፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና የመልካም ሥነ-ምግባር ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

መ) በሕግ ሙያ የሚፈለገዉን የሥራ ልምድ ያሟላ እና በዚህ አዋጅ ፈተና የሚያስፈልገዉ ከሆነ የተዘጋጀዉን ፈተና ያለፈ፤

ሠ) የክልሉን የሥራ ቋንቋ መናገር፣ ማዳመጥ፣ መጻፍና ማንበብ የሚችል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተዘረዘሩት አጠቃላይ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ በሕግ አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ የሕግ ትምህርት ለመስጠት እዉቅና ካለዉ የትምህርት ተቋም፡-

ሀ) በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቀ በኋላ በሙያዉ ስምንት ዓመት የሥራ ልምድ ያለዉ፣ ወይም

ለ) በሕግ በመጀመሪያ ዲግሪ ከተመረቀ በኋላ በሕግ ሙያ የአራት ዓመት የሥራ ልምድ ያለዉ፤ ወይም

ሐ) በሕግ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ወይም በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪና ከሕግ ጋር ተዛማጅነት ባለዉ የትምህርት መስክ ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ ከተመረቀ በኋላ ከሁለት ዓመት ያላነሰ የሥራ ልምድ ያለዉ፤

7. Requirements to Obtain Advocacy License

1/ Any applicant seeking to obtain advocacy license under this Proclamation must meet the following requirements:

A) To be an Ethiopian Citizin or Ethiopian by birth;

B) Have a minimum of diploma in Law from a recognized law school;

C) Able to present a statement from his most recent employer indicating that, in his last two years of employment, he had not been subjected to measure for disciplinary breaches and can produce proof of good conduct;

D) Meet work experience required in legal profession and who has passed the prepared examination if an exam is needed is in this proclamation;

E) Able to speak, listen, write and read the working language of the region.

2/ Without prejudice to the general principles specfied under Sub-article (1) of this Article, anyone who needs to obtain for First Level Advocacy License shall fulfill the following acadamic status from recognized institution in law:

A) Having eight years of work experience after being graduated in diploma in law; or

B) Having four years of work experience after being graduated in bachelor degree in law; or

C) Having first degree and second degree in law or first degree in law or first degree in law and second degree in related fields and not less than two years work experience after graduation;

መ) በሕግ ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ወይም በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪና ከሕግ ጋር ተዛማጅነት ባለው የትምህርት መስክ እስከ ዶክትሬት የትምህርት ዝግጅት ያለው ከተመረቀ በኋላ በሕግ ሙያ ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሥራ ልምድ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሕግ ትምህርት ለመስጠት እውቅና ካለው የትምህርት ተቋም፡-

ሀ) በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቀ በኋላ በሙያው ቢያንስ የሦስት ዓመታት የሥራ ልምድ ያለው፤ ወይም

ለ) በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናውን ያለፈ፤ ወይም

ሐ) በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ከተመረቀ በኋላ በሙያው ቢያንስ የአንድ ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ ቦርዱ የሚሰጠውን ፈተና ያለፈ መሆን አለበት፡፡

፬/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፯. ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ስር የተጠቀሰው የሥራ ልምድ በሕግ ሙያ የተገኘ ነው የሚባለው አመልካቹ ከዚህ በታች በተመለከቱት መስኮች ተሠማርቶ መቆየቱ ከታወቀ ብቻ ይሆናል፡-

ሀ) በፍርድ ቤት ዳኝነት፣ ወይም በሬጂስትራርነት፤

ለ) በዓቃቤ-ሕግነት ወይም በተከላካይ ጠበቃነት፤

ሐ) በከፍተኛ የትምህርት ወይም የሥልጠና ተቋም ውስጥ በመምህርነት፣ በአሰልጣኝነት ወይም በተመራማሪነት፤

መ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥታዊ የልማት ድርጅት፣ በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው በሚንቀሳቀሱ ሙያዊና ሕዝባዊ ማኅበራት ወይም በግል ኩባንያዎች ውስጥ በነገረ-ፈጅነት ወይም በሕግ አማካሪነት ወይም በሕግ ክፍል ኃላፊነት፤

ሠ) በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት፡፡

D) Must have from bachelor to doctrate degree in law or bachelor degree in law and upto doctorate in related field of law, and not less than one year of work experience in the legal profession after graduation.

3/ Anyone who applies for Second Level Advocacy License shall fulfill the following acadamic status from recognized institution in law:

A) Having atleast three years of experience after being graduated in diploma in law; or

B) Having first degree in law and passed the university exit exam; or

C) Having atleast one year work experience in the profession after graduation in first degree in law; or

D) An applicant who has fulfilled requirements stated from letter (A) to (C) must pass the advocacy license examination given by the board.

4/ The work experience mentioned in Article 6, Sub-Articles (2) and (3) above shall be deemed to have been acquired in the legal profession only if it is known that the applicant has been engaged in the following fields:

A) As a judge or registrar in a court;

B) As a prosecutor or defense attorney;

C) As a teacher, trainer or researcher in a higher education or training institution;

D) As an attorney or legal advisor or head of legal department in a government office, government development enterprises, professional and public associations or private companies that are legally registered at the federal or regional level;

E) As a legal clerk.

፰. ለሕግ መምህራን ስለሚሰጥ የጥብቅና ፈቃድ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ስር የተደነገገዉ ቢኖርም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምር ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሕግ መምህር በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ሌሎች መስፈርት ካሟላ የሕግ መምህርነት ሙያውን መልቀቅ ሳያስፈልገው የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጠዉ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለሕግ ትምህርት ቤት መምህር ሲሰጥ የጥብቅና ሥራው የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያስተጓጉል ስለመሆኑ መምህሩ የሚያስተምርበት ተቋም ማረጋገጥ አለበት፡፡

፱. ፈቃድ የማያሰጡ ምክንያቶች

ማንኛዉም ሰዉ የጥብቅና ፈቃድ የማይሰጠው፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮. ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፤

፪/ ታስቦ በሚፈፀም ወንጀል ወይም ከሙያ ሥነምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ እና አግባብነት ባለው ሕግ ያልተሰየመ ከሆነ፤

፫/ በሕግ አገልግሎት እንዳይሠማራ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ከሆነ ነው፡፡

፲. ፈቃድ ስለ መስጠት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የጥብቅና ፈቃድ የሚሰጠዉ በቦርዱ ነዉ፡፡

፪/ ቦርዱ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፮. መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻና ደጋፊ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ፡-

ሀ) ማመልከቻው የተሟላ ካልሆነ አመልካቹ ይህንኑ አሟልቶ እንዲቀርብ ይገልጽለታል፤

8. Licensing of Law Teachers

1/ Notwithstanding the provision of Sub-article (2) of Article 4 of this proclamation, an Ethiopian or Ethiopian-born law teacher teaching in law schools in higher education institutions may be granted advocacy license of without resigning his profession of law teacher if he meets the other requirements specified in this Proclamation.

2/ When providing legal services to a law school teacher under Sub-article (1) of this Article, the institution where the teacher teaches shall ensure that the legal work does not affect the teaching and learning process.

9. Grounds for Refusal to Grant License

No person shall be granted license:

1/ If he does not meet the requirements set forth in Article 6, Sub-Article (1) of this proclamation;

2/ If he has been convicted of a crime punishable by imprisonment for three years or more in connection with deliberate crime or professional misconduct and has not been reinstated by the relevant law;

3/ If he is prohibited by law or court from legal practice.

10. Issuance of License

1/ An advocacy license, under this proclamation, shall be issued by the board.

2/ The board after investigating a complete application and supportive documents as provided under Article 6 of this proclamation:

A) If the application is incomplete, the board shall inform the applicant to fulfill same;

ለ) ማመልከቻው ተሟልቶ የቀረበለት እንደሆነ ፈተናው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ፣ ፈተና ለማይወስዱት ደግሞ ቦርዱ ከተሰበሰበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን መስጠት አለበት፤

ሐ) የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻው በቦርዱ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ይኸው ሊገለጽለት ይገባል፤

መ) በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የውሳኔ ግልባጭ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

፫/ የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በፈቃድ ደብተር ላይ መጠቀስ ያለባቸው ነጥቦች ዝርዝር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፩. ቃለ-መሐላ ስለ መፈጸም

፩/ ማንኛዉም የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ የሚሰጠዉ ጠበቃ የሚከተለዉን ቃለ-መሐላ በጽሑፍ ያረጋግጣል፡-

"እኔ …….. ዛሬ ……… ቀን……….. ዓ.ም ከክልሉ ፍትሕ ቢሮ የክልሉን የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል የክልሉንና የሀገሪቱን ሕግጋተ-መንግሥታት እና ሌሎች ሕጎች ላከብር እና ላስከብር፣ ለፍትሕ ሥርዓቱ ተልዕኮ መሳካት በመልካም ሥነ-ምግባር በሙያዬ በቅንነት እና በታማኝነት በመሥራት የምወክላቸዉን ደንበኞቼን ጥቅም ሕግ በሚፈቅደዉ አግባብ ላስከብር፣ ከተከራካሪዎቼ እና የሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት እና በመከባበር ልሠራ እና ባለኝ እዉቀት እና ችሎታ ለሕግ የበላይነት ተገቢዉን ዕገዛ ለማድረግ ቃል እገባለሁ"፡፡

፪/ በተፈፀመዉ ቃለ-መሐላ ላይ ጠበቃዉና ቃለ-መሐላዉን ያስፈፀመዉ አካል እንዲፈርሙበት ተደርጎ በጠበቃዉ የግል ማህደር ዉስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

B) If the application is complete, the board shall issue the advocacy license within ten working days since the exam date and within five working days since meeting of the board for applicants who are not required to take an exam;

C) The board shall inform the applicant within ten working days if the application is rejected;

D) An applicant aggrieved by decision of the board can appeal to the Regional Supreme Court within thirty consecutive days since receiving copy of the decision.

3/ Particulars to be mentioned in the advocacy license certificate while issuing the advocacy license shall be determine by a directive to be issued by the board.

11. Taking Oath

1/ Any advocate to be granted an advocacy license shall ensure the following oath in writing:

"I, when taking this license from the Regional Justice Bureau, this Day on ………. Date, Month, ………..Year; I pledge to respect and protect the Regional and Federal Constitutions and other laws of the state; work with honesty and good faith to defend cases of my clients in accordance with the law, work with understanding with my opponents and colleagues, and be supportive to the rule of law with my knowledge and competence."

2/ The written oath shall be attached with the private archive of the advocate after duly signed by the advocate and the person who facilitated the oath.

፲፪. የጥብቅና ፈቃድ ወሰን

፩/ አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በክልሉ ፍርድ ቤቶችና በሌሎች የዳኝነት አካላት የስረ-ነገር ሥልጣን ስር በሚወድቁ በማናቸውም የክልል ጉዳዮች ላይ ደንበኞቹን ወክሎ መከራከር ይችላል፡፡

፪/ ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የወረዳ ፍርድ ቤቶችና በሌሎች የዳኝነት-ነክ አካላት የስረ-ነገር ሥልጣን ስር በሚወድቁ በማናቸውም የክልል ጉዳዮች ላይ የመከራከር መብት አለው፡፡

፲፫. ልዩ የጥብቅና ፈቃድ

፩/ የኅብረተሰቡን መብትና ጥቅም ለማስከበር ለሚሠሩና ለሰጡት አገልግሎት ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይቀበሉ ነፃ የሕግ አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት ቢሮው ነፃ የሕግ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፪/ ከቢሮው ልዩ የጥብቅና ፈቃድ የወሰደ አካል ፈቃዱን በየዓመቱ ማሳደስ ሳይጠበቅበት ከሐምሌ አንድ እስከ ጳጉሜ መጨረሻ ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ የሚኖርበት ሆኖ ወቅቱን ጠብቆ ሪፖርት ለቢሮው ማቅረብ ካልቻለ ፈቃዱ ይሰረዝበታል፡፡

፫/ አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተመለከተውን ቅድመ-ሁኔታ የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ሳያስፈልገው አገልግሎቱን መስጠት ይችላል፡፡ ሆኖም ይህንኑ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ አስቀድሞ ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡

12. Scope of Advocacy License

1/ First Level Advocacy License enables advocates to litigate on behalf of their clients before all matters fall under the regional courts and quasi- judicial organs jurisdiction of any regional matters.

2/ Second Level Advocacy License enables advocates to litigate on behalf of their clients before all matters fall under the Regional wereda courts and quasi-judicial organs jurisdiction of any regional matters.

13. Special Advocacy License

1/ The bureau shall grant special advocacy license to persons enabling them to provide pro bono advocacy services to protect the rights and interests of the public;

2/ Any person granted special advocacy license by the bureau is not obliged to renew the license annually; but obliged to submit report to the bureau from July 1 to the end of Pagumie; failure of which results revocation of license.

3/ Any person who has been granted First-Level Advocacy License may provide the service without the need for special advocacy license if he meets the prerequisites specified in Sub-Article (1) of this Article. However, he shall notify to the Bureau before starting to provide such services.

፬/ ነፃ የሕግ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሙያ ሥነ-ምግባርን ባለመጠበቅ ከሚፈፀሙ ግድፈቶች በመነጨ ምክንያት ፈቃዱን የመሰረዝና በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ወይም ማዕከልና ግድፈቱን የፈጸመው ግለሰብ በሕግ ተጠያቂዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

4/ Without prejudice to cancellation of the license due to professional misconduct while providing pro bono service and other administrative measureres listed in this proclamation, the licensed institution or center and individual who committed offenses may be liable to law.

፭/ ተቋማቱ ወይም ማዕከላቱ እስከ ፍርድ ቤት ድረስ በመሄድ ነፃ አገልግሎት የሰጧቸውን ግለሰቦችና ጉዳዮቹ ያስገኟቸውን ውጤቶች ያካተተ ሪፖርት ለቢሮው የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

5/ The institutions or centers are obliged to submit a report to the bureau, including the individuals they have provided pro bono services as well as the results of their cases, by going to court.

፮/ ቢሮው ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጣቸው ወገኖች ሊያሟሉት የሚገባቸውን መረጃ፣ በነፃ ፈቃድ የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራትና የባለፈቃዶችን ሥነ-ምግባር የሚወስን ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

6/ The Bureau may issue detailed directive, based on this proclamation, determining the information that parties providing pro bono legal aid services must provide, quality of services provided free of charge, and ethics of the licensees.

፲፬. <u>የፈቃድ ደረጃን ስለ ማሳደግ</u>

14. <u>Upgrading Level of Advocacy License</u>

፩/ ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ያለው ማንኛውም ጠበቃ የትምህርት ዝግጅቱም ሆነ የሥራ ልምዱ የአንደኛ ደረጃ ፈቃድ ወደሚያሰጠው ደረጃ የደረሰ እንደሆነ ደረጃው እንዲሻሻልለት ለቦርዱ ማመልከት ይችላል፡፡

1/Any advocate holding Second-Level Advocacy License may apply to the Board to upgrade his status if his educational background and work experience have reached the level required for First-Level License.

፪/ ቦርዱም መስፈርቱን አሟልቶ ለተገኘ አመልካች የተጠየቀውን አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ይወስናል፡፡

2/ The board shall then decide to grant the requested First-Level Advocacy License to an applicant who meets the requirements.

፲፭. <u>ስለ ጥብቅና ሙያ ፈተና</u>

15. <u>Advocacy License Examination</u>

፩/ ከታወቀ የሕግ ትምህርት ቤት በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ “የመውጫ ፈተናውን” ያለፈና ቢያንስ የአንድ ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም በሕግ ሙያ በዲፕሎማ ተመርቆ ከምረቃ በኋላ በሙያዉ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የሠራ ማንኛውም ሰው የሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የመመዝገቢያ ክፍያ በመፈፀም የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ ይኖርበታል፡፡

1/ Any person who has graduated with a first degree from recognized law school and passed the “exit examination” and has at least one year of work experience, or who has graduated with a diploma in law and has worked in the profession for at least three years after graduation must pass the examination to obtain Second-Level Advocacy License upon payment of a registration fee.

፪/ ፈተናውን ያላለፈ ሰው በማናቸውም ጊዜ ሌላ ፈተና መውሰድ ይችላል፡፡

፫/ ቦርዱ ዝቅተኛውን የማለፊያ ነጥብ በመወሰን ፈተናውን ካረመ በኋላ ውጤቱንና ውሳኔውን በአስር ቀናት ውስጥ ምቹ በሆነ መንገድ ሁሉ ይፋ ያደርጋል፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት
ስለ ምዝገባ እና እድሳት

፲፮. ስለ ምዝገባ

፩/ ቢሮዉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸዉን ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ ዘመናዊ በሆነ መንገድ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በምዝገባ ሥርዓቱ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ነጥቦች ቢሮው በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

፫/ ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በአዲስ ቢሮው የመዘገባቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ስም ዝርዝር በየሦስት ወሩ ጠይቆ ማግኘት ይችላል፡፡

፲፯. ከጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ጋር ስለ ሚሠሩ ሰዎች

፩/ ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ፣ የጠበቃ ረዳት ወይም ሌሎች ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን መቅጠር የሚችል ሲሆን የጥብቅና ድርጅት ከነዚህ ከተጠቀሱት ሠራተኞች በተጨማሪ ጠበቃ ሊቀጥር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቅጥር የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ቅጥሩን እንደፈጸመ ለቢሮው ማሳወቅ እና ማስመዝገብ አለበት፡፡

፫/ ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉትን በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት መቅጠር አይችልም፡-

ሀ) የጥብቅና ፈቃዱ የታገደን ወይም የተሰረዘን ሰው፤

2/ A person who has not passed the exam may take another exam at any time.

3/ After the board has determined the minimum passing score and has reviewed the exam, it shall announce the results and decision within ten days by any convenient means.

SUB-PART TWO
REGISTRATION AND RENEWAL

16. Registration

1/ The Bureau shall record a complete information of licensed advocates and law firms in a modern way.

2/ The details to be included in the registration system shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

3/ The Association may request and obtain list of the names of advocates and law firms newly registered by the Bureau, in accordance with Sub-article (1) of this Article, every three months.

17. Persons Working with Advocates or Law Firms

1/ While any advocate or law firm may employe law clerks, advocate's assistant or other supportive staff required for the work, a law firm may employ an advocate in addition to the aforementioned emplyees.

2/ An advocate or law firm that has engaged in employment pursuant to sub-article (1) of this Article shall notify same and get registered to the bureau as soon as execution of the employment.

3/ No advocate or law firm can employ the following as legal clerks; a person:

A) Whose advocacy license has been suspended or revoked;

ለ) ስሙ ከመዝገብ የተፋቀን ሰው፤

ሐ) በዲሲፕሊን ጥፋት የተባረረን ሰው፤

መ) ከሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሶ የተቀጣ እና ያልተሰየመን ሰው፤

ሠ) ቋሚ ሥራ ያለዉን ሰው፤

ረ) የሕግ ትምህርት ወይም በሕግ ሙያ የሥራ ልምድ የሌለውን ሰው፤

ሰ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሠራበት ከነበረበት ተቋም ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በዲስፐሊን ጥፋት ያልተቀጣ ስለመሆኑ እና የመልካም ሥነምግባር ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለን ሰው፡፡

፲፰. ስለ ፈቃድ እድሳት

፩/ የጥብቅና ፈቃድ በየዓመቱ ፈቃዱ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ፈቃዱን ያላሳደሰ ጠበቃ ፈቃዱ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት ፭ ተከታታይ ወራት እንደቅደም ተከተላቸው የማሳደሻ ክፍያውን ፴ በመቶ፣ ፷ በመቶ፣ ፺ በመቶ፣ ፩፻፳ በመቶ እና ፩፻፶ በመቶ ተጨማሪ መቀጫ ከፍሎ ያሳድሳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ያላሳደሰ ጠበቃ የጥብቅና ፈቃዱ ታግዶ በቢሮው እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ፈቃዱን ያላሳደሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ ካቀረበ በቀጣዩ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማሳደሻ ክፍያውን ፴ በመቶ ተጨማሪ መቀጫ ከፍሎ የጥብቅና ፈቃዱ ሊታደስለት ይችላል፡፡

B) Whose name has been struck off from register;

C) who has been dismissed dueto disciplinary offense;

D) Who has been convicted of crime related to ethics and has not been reinstated;

E) Who has a permanent job;

F) Who does not have legal education or experience in the legal profession;

G) Who is failed to provide evidence of not being convicted of disciplinary offense and good conduct assurance from the recent institution he was working two years before leaving.

18. Renewal of License

1/ An adocacy license shall be renewed annually within one month from the last day of its validity;

2/ An advocate who fails to renew his license within the time limit specified in Sub-article (1) of this Article in the absence of any force majeure; may renew his license within five consecutive months from the last day of the validity of his license, paying an additional fine of 30 percent, 60 percent, 90 percent, 120 percent and 150 percent of the renewal fee, respectively.

3/ An advocate who fails to renew his license within the period specified in Sub-article (2) of this Article, his license shall be suspended and detained by the bureau.

4/ Without prejudice to the provision of Sub-article (3) of this Article, if the advocate or law firm provides convincing evidence that the failure to renew his license was due to force majeure, his license may be renewed within the next one month from submission of the evidence by paying an additional fine of 30 percent of the renewal fee.

፲፱. ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርቡ ማስረጃዎች

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃዱን ለማሳደስ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

፩/ የታክስ ክሊራንስ ወይም የጥብቅና ድርጅት አባል ከሆነ ከድርጅቱ ይህንኑ ማቅረብ፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት አስገዳጅ የሕግ ሥልጠና ከተራዘመለት ጠበቃ በስተቀር ጠበቃዉ በዚህ አዋጅ የተቀመጠዉን የሥልጠና ግዴታ ማጠናቀቁን የሚገልጽ ማስረጃ፤

፫/ ለጠበቆች ማኅበር መክፈል የሚጠበቅበትን የአባልነት መዋጮ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ከማኅበሩ የሚሰጥ ማስረጃ፤

፬/ እድሜዉ ከሰባ ዓመት በላይ የሆነ ጠበቃ ሕጋዊ ከሆነ የጤና ተቋም የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ ያለ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ፤

፭/ በዓመት ውስጥ መስጠት የሚጠበቅበትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ስለመስጠቱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤ እና

፮/ የጸና የመድህን ዋስትና ማስረጃ፡፡

፳. ፈቃድ ስለ መመለስና መልሶ ስለ መውሰድ

፩/ ማንኛውም ጠበቃ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የጥብቅና ፈቃዱን ለቢሮው መመለስ አለበት፡-

ሀ) ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በቋሚነት የተሠማራ እንደሆነ፤

ለ) የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ፤

ሐ) የጥብቅና አገልግሎት ለማቆም ከወሰነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጠበቃዉ ፈቃድ ለመመለስ ሲያመለክት ቢሮው የጥብቅና ፈቃድ ደብተሩን ወዲያውኑ መረከብ አለበት፤ ሆኖም ጠበቃው የጥብቅና አገልግሎቱን ማቋረጡን የሚገልጽ ማስረጃ ለጠበቃው የሚሰጠው ጠበቃው ከሚመለከተው አካል የግብር ክሊራንስ ይዞ ሲቀርብ ይሆናል፡፡

19. Documents Submitted for License Renewal

Any advocate or law firm shall submit the following evidences to renew his advocacy license:

1/ Tax clearance; or if he is partner of a law firm, submitting same from the firm;

2/ A document stating the advocate has completed the training obligation set forth in this proclamation except for an advocate whose compulsory legal training has been extended in accordance with Article 29, Sub-article (4) of this proclamation;

3/ A document from the association confirming he or has paid the membership fee required to be paid to the Bar Association;

4/ If the advocate is over seventy years of age, a certificate from legal health institution stating he is in a health condition that allows him to provide legal services;

5/ Proof of providing free legal services that are expected to be provided within a year; and

6/ Proof of valid insurance.

20. Returning and Retaking License

1/ Any advocate shall return his advocacy license to the bureau when encountering the following conditions:

A) When he is permanently engaged in any job other than advocacy service;

B) When he is unable to render advocacy service;

C) When he decides to terminate advocacy service.

2/ When an advocate applies to return his license pursuant to Sub-article (1) of this Article, the bureau shall immediately receive the advocacy license certificate. However, evidence of termination advocacy service shall be provided to the advocate when he brings tax clearance certificate.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃዱን የመለሰ ጠበቃ ወደ ጥብቅና ሥራው መመለስ ከፈለገ ፈቃዱን መልሶ ሊወስድ ይችላል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም ጠበቃው ከሕግ ሙያ ውጪ ከሦስት ዓመት በላይ ተለይቶ ከቆየ ፈቃዱ የሚመለስለት ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ወስዶ ካለፈ ብቻ ነው፡፡

ክፍል ሦስት

የጠበቆች የሙያ ግዴታ

ንዑስ-ክፍል አንድ

ጠቅላላ የጠበቆች ግዴታ

፳፩. ከጥብቅና ፈቃድ ጋር የተያያዘ ግዴታ

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

፩/ በደንበኛ፣ በፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም አግባብ ባለው አካል የጥብቅና ፈቃዱን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት፤

፪/ የጥብቅና ፈቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ወይም መገልገያ አሳልፎ ያለመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፳፪. ስለ ጥብቅና አገልግሎት ውል እና ተያያዥ ግዴታዎች

፩/ ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሚሰጠው የሕግ ምክር አገልግሎት ውጭ ከደንበኛው ጋር የሚያደርገውን የጥብቅና አገልግሎት ውል በጽሑፍ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የጥብቅና አገልግሎት ውሉ ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ የገንዘብ ክፍያ፣ የአከፋፈሉን ስልት እና ጊዜ፣ ጠበቃዉ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን የጥብቅና አገልግሎት የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

3/ An advocate who returned his advocacy license pursuant to Sub-article (1) of this Article, may get his license back if he wants to resume to his advocacy service.

4/ Notwithstanding to the provision of Sub-article (3) of this Article, an advocate who dissociated himself from advocacy service for more than three years can get back his license only when he passes entrance examination given for his level of license.

PART THREE

ADVOCATES' PROFESSIONAL OBLIGATION

SUB-PART ONE

GENERAL OBLIGATION OF ADVOCATES

21. Obligations Related with Advocacy License

Any advocate or law firm has an obligation to:

1/ Show his advocacy license when requested by a client, court or any appropriate body;

2/ Not to give his license for others to make use of it or get benefit out of it.

22. Contract of Advocacy Service and Related Obligations

1/ Any advocate or law firm shall make the advocacy service contract with his client in writing except legal advice he provides for short period of time.

2/ The contract of the advocacy service shall include the total amount of fee the client has to pay to the advocate, system and time of payment and advocacy service the advocate has to provide on the case.

፫/ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

ሀ) ለጥብቅና አገልግሎት መስጫ የሚሆን ቢሮ የማሟላት፤

ለ) የጥብቅና ሥራን በአገናኝ ያለመሥራት፤ እና

ሐ) የጥብቅና ውልን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ማቋረጥ እና በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የክፍያ መጠን በላይ ተጨማሪ ክፍያ ከደንበኛ ያለመጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡

፳፫. ስለ ታማኝነትና ለፍትሕ አጋር መሆን

፩/ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ሥራውን በታማኝነት የመሥራትና ለፍትሕ አጋር የመሆን ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፦

ሀ) ያለበቂ ምክንያት ጉዳይን ያለማጓተት፤

ለ) ምስክሮችን በሐሰት ያለማደራጀት፤

ሐ) ሐሰተኛ ማስረጃ ያለማቅረብ ወይም ያለማስቀረብ፤

መ) ተዘጋጅቶ የመቅረብና ተገቢውን ክርክር የማድረግ፤

ሠ) የሕግ መሠረት የሌለውን ጉዳይ ያለመያዝ፤

ረ) የደንበኛውን ወይም ባለጉዳዩን ምስጢር ያለማውጣት፤

ሰ) በሥራው ዙሪያ ለመመካከር በቢሮው በሚጠራ የምክክር መድረክ ላይ ተገኝቶ የመሳተፍ፤ እና

ሸ) ሌሎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚገለጹ የሥነ-ምግባር ግዴታዎች አሉበት፡፡

ንዑስ-ክፍል ሁለት

የሕግ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ

፳፬. ዓላማ

የሕግ ሥልጠና ዓላማ ጠበቆች የሙያ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ወቅታዊ ዕውቀትና ክህሎት በቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

3/ Any advocate or law firm has an obligation:

A) To fulfill a buearu used to provides advocacy service;

B) Not providing advocacy service with intermediary;

C) Not to terminate the advocacy service contract with out suffient and legal cause and not to demand more payment than mentioned in the advocacy contract.

23. Honesty and Cooperate to Justice

1/ Any advocate or law firm has an obligation to perform his advocacy service honestly and cooperate to justice.

2/ Without prejudice to the general provision of Sub-article (1) of this Article, any advocate or law firm has an obligation:

A) Not to delay cases with out enough reason;

B) Not to organize false witnesses;

C) Not to produce or cause production of false evidence;

D) To appear preparedly and make appropriate litigation;

E) To reject cases which have no legal basis;

F) To keep confidenciality of his client’s information;

G) To participate in dialogue forums called by the bureau regarding his advocacy profession;

H) To respect other code of conducts to be determined by a regulation following this proclamation.

SUB-PART TWO

OBLIGATION TO TAKE LEGAL TRAINING

24. Objective

The objective of legal training is to enable advocates to acquire sustainable up-to-date knowledge and skill to discharge their professional responsibility.

፳፭. የሕግ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ

፩/ ማንኛውም ጠበቃ በማኅበሩ የሚዘጋጅ የሕግ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የሕግ ሥልጠናው በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ሊሰጥ የሚችል ይሆናል፡፡

፫/ በሕግ ሥልጠና የሚሸፈኑ የሥልጠና ዘርፎችን፣ የሥልጠና ጊዜውን ርዝመት፣ አጠቃላይ የሥልጠና አሰጣጥ መርሃ-ግብር፣ የሥልጠና ክፍያ እና ሌሎች ከሥልጠና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ከቢሮው ጋር በመመካከር ማኅበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፬/ የሕግ ሥልጠናው በዋናነት፡-

ሀ) ተግባር እና ንድፈ-ሐሳብ ላይ ያተኮረ መሠረታዊ እና ሥነ-ሥርዓታዊ ሕጎች ሥልጠና፤ እና

ለ) እንደ አስፈላጊነቱ የጠበቆች አሠራር እና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ሥልጠናዎችን ያጠቃልላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገዉ ቢኖርም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አካላት የሕግ ሥልጠና እንዲወስዱ አይገደዱም፡-

ሀ) በዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ ያለ የጥብቅና ፈቃድ ያለዉ የሕግ መምህር፤

ለ) የሕግ ሥልጠና የሚሰጥ ጠበቃ ሥልጠናዉን ለሰጠበት ዓመት፡፡

፳፮. ዕውቅና ስለ ተሰጣቸው ተቋማት

፩/ የሕግ ሥልጠና የሚሰጠው በማኅበሩ እውቅና በሚሰጠው ተቋም ይሆናል፡፡

፪/ ማኅበሩ ለተቋሙ ዕዉቅና ከመስጠቱ በፊት የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶችን ቀድሞ ማፅደቅ ይኖርበታል፤ ሆኖም በቅድሚያ የጸደቁት የሥልጠና ዓይነቶች በማኅበሩ ወደፊት ሊሻሻሉ፣ ሊታገዱ ወይም ሊሰረዙ ይችላሉ፡፡

25. Obligation to Take Legal Training

1/ Any advocate has an obligation to take legal training prepared by the association.

2/ The legal training may be offered continuously or at different times.

3/ Training areas to be covered by the legal training, duration of the training, general schedules of the training, training fees and other issues related with training shall be determined by a directive to be issued by the Association in consulation with the bureau.

4/ The legal training mainly includes:

A) Substantive and procedural laws focused on practical and theoretical concepts, and

B) As deemed as necessary, advocates working procedure and professional ethics.

5/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, the following persons shall not be obliged to take legal training:

A) University law lecturer who has advocacy license;

B) An advocate who provides the training for that same year.

26. Accredited Institutions

1/ Legal training shall be rendered by an institution accredited by the association.

2/ The association shall approve the training type before providing recognition to the institution; however, priorly approved training types may be amended, suspended or revoked by the association.

፫/ የተከታታይ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎች ዕውቅና የሚያገኙበት ሥነ-ሥርዓት እና መሥፈርትን በተመለከተ ማኅበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፯. ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት

፩/ የሥልጠና ተቋሙ በሥልጠና ላይ ያሉትን ሠልጣኞች ሥልጠና ከጀመሩበት እንዲሁም ሥልጠና ያጠናቀቁ ሠልጣኞችን ሥልጠናውን ካጠናቀቁበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለማኅበሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ማንኛዉም ጠበቃ ማኅበሩ ባሳወቀው የሥልጠና ጊዜ ለመሠልጠን የማያስችል በቂ ምክንያት ካለው ምክንያቱን ለማኅበሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፳፰. የሕግ ሥልጠና አለመከታተል

፩/ ማንኛዉም ጠበቃ በዚህ ንዑስ ክፍል የተቀመጡትን የሕግ ሥልጠና ግዴታዎች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ማኅበሩ ይህንኑ ለቢሮው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ቢሮው ከተከታታይ የሥልጠና ግዴታ ጋር ተያይዞ ያለበቂ ምክንያት የሥልጠና ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ያልሆነ ጠበቃን የድሲፕሊን ክስ ሊመሰርትበት ይችላል፡፡

፳፱. የሕግ ሥልጠና ግዴታን ስለ ማራዘም

፩/ ማንኛውም ጠበቃ በአሳማኝ ምክንያት ማኅበሩ በሚያወጣው የሥልጠና ጊዜ ውስጥ ሥልጠናውን መውሰድ ካልቻለ ጠበቃው ሥልጠናውን ማኅበሩ ባወጣው ጊዜ ውስጥ መውሰድ ስላለመቻሉና የሥልጠና ጊዜው እንዲራዘምለት ማኅበሩ ከያዘው የሥልጠና ጊዜ ከአንድ ወር በፊት ቀድሞ ለማኅበሩ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ Procedure and criterion to continuous legal training providers shall be determined by a directive to be issued by the association.

27. Responsibility to Report

1/ The training institution shall report to the association about on training trainees within one Month since the commencement of the training as well as training completed trainees since the time of completion of the training.

2/ Any Advocate who is unable to take the training on the program set by the association due to sufficient reason shall notify in writing this to the association.

28. Failure of Taking Law Training

1/ If any advocate fails to comply with the training obligations provided in this part, the Association shall notify this fact in writing to the bureau.

2/ The bureau may charge, for the violation of disciplinary rules, an advocate who, without good cause, is not willing to comply with his mandatory continuous training.

29. Extending Mandatory Law Training

1/ If any Advocate, for good cause, is unable to take the training within the period scheduled by the association, he has to notify this, one month in advance, by a written application to the Association so that the training to be extended to him.

፪/ ጠበቃዉ የሥልጠና ጊዜዉ እንዲራዘምለት የሚያቀርበዉ ማመልከቻ ሥልጠናዉን መዉሰድ እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት፣ ሥልጠናዉን ለመዉሰድ ያደረገውን ጥረት እና በቀጣይ መቼና በምን አግባብ እንደሚወስድ ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፫/ ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረበለት ማመልከቻ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው የሥልጠና ጊዜውን በዚያው ዓመት ውስጥ ጠበቃው በጠየቀው ጊዜ ወይም እራሱ በመሰለው ጊዜ ሊቀይርለት ይችላል፤ ማኅበሩ ጥያቄዉን ከተቀበለዉ የቅያሬውን ሁኔታ ወይም ጥያቄውን ካልተቀበለው ያልተቀበለው መሆኑን በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለጠበቃው ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ጠበቃው በዓመት መውሰድ የሚጠበቅበትን የሕግ ሥልጠና ግዴታ በዚያው ዓመት አጠቃሎ መውሰድ ካልቻለ እና ሥልጠናዉን ያልወሰደዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበና ማኅበሩ ካመነበት ጠበቃው ያልወሰደውን የሥልጠና ጊዜ ወደ ቀጣይ ዓመት በማሸጋገር በቀጣይ ዓመት መውሰድ ከሚጠበቅበት የሥልጠና ግዴታ ጋር ደርቦ እንዲወስድ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

ንዑስ-ክፍል ሶስት
ስለ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ

፴. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ

፩/ ማንኛዉም በጥብቅና ድርጅት ዉስጥ ሽሪክ ሆኖ ወይም ተቀጥሮ የሚሠራ ጠበቃ ወይም በግሉ የሚሠራ ጠበቃ እንደጉዳዩ ፍሰት እየታየ በዓመት ከሶስት ጉዳይ ያላነሰ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰጠዉም፡-

ሀ) የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሰዎች፤

2/ The training extension application which the advocate submits shall specify the reasons why he was not able to take the training in due time, the effort he made to take the training and his plan as to when and how he would take the training in the future.

3/ If the Association finds the application submitted based on Sub-article (2) of this Article is convincing, it may rescheduled the program based on the advocate's request or as it may deem necessary any time with in the same year. If the Association accepts the request, it shall notify the advocate in writing the extension it has made or the rejection of the request within 15 consecutive days.

4/ If it is not possible for the advocate to take the training in that same year due to force majeure and same is supported by evidence and such reasons have convinced the Association, then the Association may permit the advocate to take the training in the following year in addition to the training he is expected to take in that same year.

SUB-PART THREE
OBLIGATION TO PRO BONO ADVOCACY SERVICE

30. Obligation to Provide Pro Bono Advocacy Service

1/ Any advocate who works in law firm being either as a partner or as an employee has an obligation to provide pro bono advocacy service, for not less than three cases in a year, based on the case load. And the service shall be provided to the following persons:

A) To those who can not afford to pay;

ለ) በኤች አይ ቪ ቫይረስ ምክንያት ወላጆቻቸውን አጥተው ለአካለ-መጠን ላልደረሱና ከፍለው መከራከር ለማይችሉ ልጆች ወይም በዚሁ በሽታ ምክንያት ልጆቻቸውን አጥተው በእድሜ ለገፉ ከፍለው መከራከር ለማይችሉ ወላጆች፤

ሐ) በምርምር፣ በስፖርት፣ በማስተማር፣ በፈጠራ ሥራ፣ በጦርነት ጀብድ በመሥራት እና በሌሎች መስኮች ተሳትፈው ሀገርን ያስጠሩ ሰዎች መሆናቸው በክልሉ መንግሥት እውቅና ለተሰጣቸው፤

መ) ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ለሲቪክ ማኅበራት እና ለማኅበረ-ሰብ ተቋማት፤

ሠ) ሕግን፣ የሕግ ሙያን እና የፍትሕ ሥርዓቱን ለማሻሻል ለሚሠሩ ኮሚቴዎች እና ድርጅቶች፤

ረ) ፍርድ ቤት ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቅላቸዉ ሰዎች ነዉ፡፡

፪/ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሕዝብ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታውን መወጣቱን የሚገልጽ ማህደር መያዝ የሚኖርበት ሲሆን ማህደሩም እያንዳንዱ አገልግሎት የተሰጠበትን ቀን፣ ዓይነቱን እና የወሰደውን ጊዜ የሚገልጽ አስፈላጊ ከሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

፴፩. ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ስለ መምራት

፩/ ቢሮው እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነፃ የጥብቅና አገልግሎት መጠን ሳያንስ በነፃ የጥብቅና አገልግሎት ሊስተናገዱ የሚገባቸውን ጉዳዮች እያጣራ ለጠበቆች ይመራል፡፡

፪/ እያንዳንዱ ጠበቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በቢሮው የሚመራለትን የነፃ ጥብቅና አገልግሎት ተቀብሎ የመሥራት ግዴታ አለበት፤

B) To minors who lost their parents by HIV and can not litigate paying for the advocacy service; and to aged individuals who lost their children by HIV and can not litigate paying for the advocacy service;

C) To individuals who are given recognition by the regional government for significant contribution in research, sport, education, innovation, war and other fields;

D) To charity organizations, civic societies and community institutions;

E) To committees and organizations working for improvement of law, legal profession and justice system;

F) To persons whom court requests the provision of pro bono asdvocacy service.

2/ Every advocate or law firm has to keep record of its pro bono service to the public and such record shall contain details about the data when each service was provided, type and the time the case took.

31. Assigning Pro Bono Service

1/ The bureau shall, without lessening the limit each advocate should render pro bono advocacy service in a year, identify and assign pro bono cases to advocates.

2/ Each Advocate shall have an obligation to receive the pro bono advocacy services referred to him by the bureau based on Sub- article (2) of this Article and render the service.

፫/ ቢሮው የነጻ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ የመራለትን ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት መፈጸሙን መቆጣጠር እና መከታተል አለበት፡፡

ንዑስ-ክፍል አራት

መድን እና የደንበኞች ንብረት

፴፪. የሙያ ኃላፊነት መድን የመያዝ ግዴታ

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሥራውን በአግባቡ ሳይወጣ በመቅረቱ ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ካሳ የሚሆን የሙያ ኃላፊነት መድን ጥብቅና ፈቃዱን ባወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ መያዝ አለበት፡፡

፴፫. የመድን ሰጪው ግዴታዎች

፩/ ለጠበቃ ወይም ለጥብቅና ድርጅት የሙያ ኃላፊነት መድን የሰጠ መድን ሰጪ የመድን ውሉ ሲቋረጥ ወይም ግዴታው እንዳይፈፀም ሊያደርግ የሚችል ሁኔታ ሲፈጠር ሁኔታውን ወዲያውኑ ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ መድን ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጠውን ግዴታውን ባለመወጣቱ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

፴፬. የደንበኛን ንብረት ስለ ማስተዳደር

ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

፩/ ከሙያ ሥራው ጋር በተገናኘ በይዞታው ወይም በአስተዳደሩ ሥር የሚገኝን የደንበኛው ወይም የሦስተኛ ወገንን ንብረት አስተዳደርን ጥበቃ ከራሱ ንብረት ፍጹም በማይገናኝበት ሁኔታ ለይቶ ማስተዳደር አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱትን የደንበኛው ወይም የሦስተኛ ወገን ንብረቶች የሚመለከቱ ማናቸውንም ሰነዶች ጉዳዩ ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

3/ The bureau shall control and monitor whether an advocate or law firm has implemented the pro bono advocacy service the bureau has referred or not based on this proclamation.

SUB-PART FOUR

INSURANCE AND CLIENTS' PROPERTY

32. Obligation to Secure Professional Indemnity Insurance

Every advocate or law firm shall secure a professional indemnity insurance policy within one year from taking the advocacy license, for the damage he/it may cause on his/its client due to failure to discharge the duty properly.

33. Obligation of Insurers

1/ An Insurer which has sold a professional indemnity insurance to an advocate or law firm shall have the obligation immediately report to the bureau when the contract is terminated or when circumstance arises that prevent the performance of the contract.

2/ The insurer shall be liable for damages that may be caused due to its failure to report as provided under Sub-article (1) of this Article.

34. Administration of Client's Property

Any advocate or law firm:

1/ Shall administer and keep his client's or third party's property, which he possessed in the course of discharging his duty, separetly from his own property;

2/ Has an obligation to keep documents related with properties of his clients' or properties of third parties' specified in Sub-article (1) of this Article up to five years from the time when the case has got its completion.

፴፭. የደንበኛ የአደራ ሒሳብ

፩/ በጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እጅ የሚገኝ የደንበኛ ገንዘብ ከጠበቃው ወይም ከጥብቅና ድርጅቱ በተለየ ሒሣብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

፪/ ቢሮው ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች የደንበኞች አደራ ሒሳብ ለመያዝ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ የደንበኛውን የአደራ ሒሳብ በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ማንቀሳቀስ የሚቻለው ክፍያ ሊፈፀምባቸው የሚገቡ ሥራዎች መከናወናቸውን እና በደንበኛው ስም መደረግ ያለባቸው ወጪዎች በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

፬/ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ የደንበኛ ወይም የሦስተኛ ወገን ጥቅም ያለበት ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ሲቀበል ለደንበኛው ወይም ለሦስተኛ ወገን ወዲያው ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ወይም በሕግ ወይም ከደንበኛው ጋር በተደረገ ስምምነት ካልተፈቀደ በስተቀር አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለክፍያ ያልዋለ በአደራ ሒሳብ ውስጥ የተቀመጠን ገንዘብ ደንበኛው ወይም መብት ያለው ሦስተኛ ወገን ሲጠይቅ ወይም ጉዳዩ ሲጠናቀቅ ወዲያውኑ ከበቂና የተሟላ ሪፖርት ጋር ማስረከብ አለበት፡፡

ክፍል አራት

ስለ ጥብቅና ድርጅት

፴፮. የጥብቅና ድርጅት ስለ ማቋቋም

በዚህ አዋጅ መሠረት የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ጠበቆች አንድ ላይ በመሆን የጥብቅና ድርጅት ማቋቋም ይችላሉ፡፡

፴፯. የአገልግሎት ወሰን

፩/ የጥብቅና ድርጅት ዋነኛ ተግባር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ነው፡፡

35. Trust Account of a Client

1/ Client's money which is under possession of an advocate or law firm shall be kept in different account from the advocate's or law firm's private account.

2/ The bureau may determine requirements that advocates or law firms must fulfill to keep their clients' trust account by a directive.

3/ The advocate or law firm can only transact his client's trust account and pay money when activities, which need payment, are undertaken and the expenses are supported by evidences issued in the name of the client.

4/ The advocate or law firm shall immediately notify the situation to his client or third party when he/it receives money or other property that involves the interest of the client or third party.

5/ Without prejudice to allowing by this proclamation or relevant law or agreement made with the client, an advocate or law firm shall promptly handover unpaid money kept in the trust account along with sufficient and full report upon request of the client or third party or upon completion of the case.

PART FOUR

LAW FIRM

36. Establishment of Law Firm

According to this Proclamation, at least two or more advocates who hold a valid advocacy license may form an advocacy firm together.

37. Scope of Service

1/ The primary function of a law firm is providing advocacy services.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከጥብቅና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች አገልግሎቶች ሊሰጥ ይችላል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን አዋጅ ለመፈፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፴፰/ የጥብቅና ድርጅት አደረጃጀት እና ኃላፊነት

፩/ የጥብቅና ድርጅት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር አደረጃጀት ይኖረዋል፤

፪/ የጥብቅና ድርጅት፡-

ሀ) ውል ማዋዋል፤

ለ) የንብረት ባለቤት መሆን፤

ሐ) በስሙ መክሰስና መከሰስ፤ እና

መ) የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት የሚኖረው ሌሎች መብቶችና ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡

፫/ የጥብቅና ድርጅት ሽሪኮች ለሶስተኛ ወገን የሚኖርባቸው ኃላፊነት በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ባላቸው የመዋጮ ድርሻ ልክ የተወሰነ ይሆናል፤

፬/ የጥብቅና ድርጅት አባላትን የሚመለከት ለውጥ ቢመጣም የጥብቅና ድርጅት ኅልውና ይቀጥላል፤

፭/ የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት መስጠቱ በኢትዮጵያ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሕጎች መሠረት አገልግሎቱን የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ሥራ አያሰኘውም፡፡

2/ Without prejudice to the provision of Sub-article (1) of this Article, a law firm may provide other services related to advocacy services; detailed implementations shall be determined by a directive to be issued by the Bureau for the implementation of this Proclamation.

38. Organizational Structure and Responsibilities of Law Firm

1/ The organizational structure of a law firm shall be limited partnership;

2/ A law firm shall:

A) Make contract;

B) Own property;

C) Sue and be sued on its own name; and

D) Have other rights and obligations which another legal organization has.

3/ The liability of partners of a law firm to third parties shall be limited to the amount of their contribution to the law firm;

4/ The law firm shall continue to exist despite changes on the membership of the law firm;

5/ The provision of advocacy services by a law firm does not make the service a business or investment as defined under the Ethiopian Commercial Code and Investment Laws.

፴፱/ ስለ ጥብቅና ድርጅት ስያሜ

፩/ የጥብቅና ድርጅት አባላት ማንኛውም ስያሜ የጥብቅና ድርጅቱ መጠሪያ እንዲሆን መምረጥ እና መወሰን ይችላሉ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ለጥብቅና ድርጅቱ መጠሪያነት የተመረጠው ስም በቢሮው በሚከተሉት ምክንያቶች ተቀባይነት ላይኖረዉ የሚችለዉ፡-

ሀ) ከሌላ የጸና የጥብቅና ድርጅት ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፤

ለ) ደንበኞች ድርጅቱን ከሌላ የጥብቅና ድርጅት በቀላሉ መለየት እንዳይችሉ በሚያደርግ መልኩ ሊያሳስት ወይም ሊያደናግር የሚችል ከሆነ፤ ወይም

ሐ) ለሕግ ወይም ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆነ ነው፡፡

፫/ የጥብቅና ድርጅት ስም የጥብቅና ድርጅት መሆኑን የሚያመለክትና ከስሙ በስተመጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር" ወይም ("ኃ.የተ.የሽ.ማ") የሚል ሐረግ ያለው መሆን አለበት፤

፬/ በጥብቅና ድርጅቱ ስም የሚወጡ ሰነዶች በሙሉ በግልጽ ስሙን እና **"ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር"** የሚለውን ሐረግ መያዝ አለባቸው፡፡

፵. የመቋቋሚያ መሥፈርት እና ሥነ-ሥርዓት

፩/ የጥብቅና ድርጅት በቢሮው በመመዝገብ ይቋቋማል፡፡

፪/ የጥብቅና ድርጅት ለማቋቋም የሚከተሉት ሰነዶች ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) የአባላቱን ሙሉ ስምና ፊርማን የያዘ ማመልከቻ፤

ለ) የድርጅቱን መመሥረቻ ጽሑፍ፤

ሐ) የሽሪኮቹን የጥብቅና ፈቃድ ቅጂ፤

መ) አባላት ድርጅቱን ለመመሥረት የተስማሙበትን የሽርክና ስምምነት፤

39. Naming of Law Firm

1/ Members of a law firm may choose and decide any name to be their firm's name.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, the name chosen for name of the law firm may not be accepted by the Bureau for the following reasons:

A) If it is similar to name of another valid existing law firm;

B) If it is likely to mislead or confuse clients in a way that prevents them from easily distinguishing the firm from another law firms; or

C) If it is contrary to law or public morals.

3/ Name of the law firm must indicate that it is a law firm and must end with the phrase "Limited Liability Partnership" or ("LLP");

4/ All documents issued in the name of the law firm must clearly contain the name and the phrase "Limited Liability Partnership."

40. Establishment Requirements and Procedures

1/ A law firm shall be established upon registration by the bureau.

2/ The following documents shall be submitted with the application for the establishment of a law firm:

A) An application containing full names and signatures of the members;

B) Memorandum of Association of the firm;

C) Copies of the advocacy license of partners;

D) Partnership agreement by which members agreed to form the firm;

ሠ) በምሥረታ ሂደት ድርጅቱን የሚወክለዉ አባል የተሰየመበት ቃለ-ጉባኤ፡፡

፫/ የጥብቅና ድርጅት መመሥረቻ ጽሑፍ በንግድ ሕጉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር መመሥረቻ ጽሑፍ ሊያካትታቸዉ የሚገቡ ዝርዝር ጉዳዮችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

፬/ በቢሮው የሚመለከተው የሥራ ክፍል የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸዉን ካረጋገጠ ማመልከቻውን በተቀበለ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ የጥብቅና ድርጅቱን በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፭/ በቢሮው የሚመለከተው የሥራ ክፍል የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጎች ጋር የሚጣረሱ ናቸው ብሎ ካመነ ማመልከቻውን በተቀበለ በ፳ የሥራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ማድረግና ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን መነሻ የሆነውን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔ በተሰጠው በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔ በተሰጠው በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፵፩. የመዋጮ ዓይነትና መጠን

፩/ የጥብቅና ድርጅት አባላት ዋነኛው መዋጮ ክህሎት መሆን አለበት፡፡

፪/ አባላት መዋጮዎችን በገንዘብ ወይም በዓይነት ማዋጣት ይችላሉ፡፡

E) Minute in which representative of the firm is nominated in the process of establishment.

3 The memorandum association of a law firm shall contain particulars stated in the commercial code which memorandum of association of Limited Liability Partnership should contain.

4/ The relevant department in the bureau, after verifying that the documents submitted to it are in compliance with the requirements of this proclamation and other relevant laws, shall, within 15 working days of receiving the application, register the firm and issue certificate of registration.

5/ If the relevant department of the Bureau believes that the documents submitted to it are in violation of this Proclamation and other relevant laws, it shall reject the application within twenty working days of receiving it and shall notify the applicant in writing stating the reason for the rejection of the application.

6/ A person who is agrived by a decision given pursuant to Sub-article (5) of this Article, may file an appeal to the board within Fifteen working days since the dicision is given.

7/ A party aggrieved by a decision made pursuant to Sub-article (6) of this Article may file an appeal to the Supreme Court of the Region within thirty working days of the date of the decision.

41. Type and Amount of Contributions

1/ The primary contribution of members of a law firm shall be in the form of skills.

2/ Members may make contributions in cash or in kind.

፫/ የጥብቅና ድርጅት አባላት የመዋጮ መጠን የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት የሚበቃ መሆን ያለበት ሆኖ የእያንዳንዱ አባል የገንዘብ መዋጮ ከሀምሳ ሺህ ብር ማነስ የለበትም፡፡

፬/ ገንዘብ ባልሆነ ማናቸውም መንገድ በጥብቅና ድርጅት አባል የሚደረግ መዋጮ ዋጋ በሁሉም አባላት ስምምነት እና አግባብነት ባላቸው ሕግጋትና ደንቦች ይወሰናል፡፡

፵፪. የአባላት መብትና ግዴታ

፩/ የጥብቅና ድርጅት አባል የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

ሀ) በጥብቅና ድርጅቱ ስብሰባዎች የመካፈል እና ድምጽ የመስጠት፣

ለ) በድርሻው መጠን ከጥብቅና ድርጅቱ ትርፍ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው ወይም ከሚተርፈው የማኅበሩ ሀብት የመካፈል፣

ሐ) የጥብቅና ድርጅቱን አጠቃላይ አሠራር የመከታተልና የማወቅ፣

መ) በሽርክና ስምምነት፣ በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱ ወይም ከጥብቅና ድርጅቱ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች መብቶችና ጥቅሞችን የመጠቀም፡፡

፪/ የጥብቅና ድርጅት አባል የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

ሀ) ለጥብቅና ድርጅቱ መክፈል የሚጠበቅበትን መዋጮ በወቅቱ መክፈል፣

ለ) በማናቸውም ጊዜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት በትጋት የመሥራት፣

ሐ) ለራሱ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም ባይሆንም የጥብቅና ድርጅቱን ጥቅም ከሚጻረሩ ድርጊቶች ወይም ኃላፊነትን ከሚያጓድሉ ተግባራት መታቀብ፣ እና

3/ The amount of contributions by members of a law firm shall be sufficient to achieve objectives of the firm, and the financial contribution of each member shall not be less than fifty thousand birr.

4/ The amount of any non-monetary contribution made by member of a law firm shall be determined by agreement of all members and in accordance with relevant laws and regulations.

42. Rights and Obligations of Members

1/ Member of a law firm shall have the following rights:

A) To participate in meetings of the law firm and to vote;

B) To participate in profits of the law firm or in the assets of the association that are collected or left over in the event of the law firm's bankruptcy, in proportion to his share;

C) To monitor and be aware of the general operations of the law firm;

D) To enjoy other rights and benefits provided for in the partnership agreement, this Proclamation and other relevant laws, or arising from the nature of the law firm.

2/ Member of a law firm shall have the following obligations:

A) To pay the dues to the law firm on time;

B) To work diligently at all times to achieve objectives of the law firm;

C) To refrain from any actions that are contrary to interests of the law firm or that impair responsibilities whether or not they are for his own benefit, and

መ) በሽርክና ስምምነት፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱ ወይም ከድርጅቱ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች ግዴታዎችን የመወጣት::

፵፫. ትርፍ እና ኪሣራ ክፍፍል

በጥብቅና ድርጅቱ የሽርክና ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የድርጅቱ አባላት የድርጅቱን ትርፍ እና ኪሳራ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው የማኅበሩ ሀብት የሚተርፈውን ሀብት በድርጅቱ ዉስጥ ባላቸዉ ድርሻ መጠን የመካፈል መብት አላቸው::

፵፬. የድርጅቱ አባላት ለውጥ

፩/ አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተጣለው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅቱን ለሚለቅ አባል የድርሻው ዋጋ እና የትርፍ ድርሻው ሊከፈለው ይገባል፤

፪/ የጥብቅና ድርጅት አባል በሚሞት ጊዜ አባሉ ሊከፈለዉ የሚገባ ያልተከፈለዉ የትርፍ ድርሻ ለሕጋዊ ወራሾቹ ይተላለፋል::

፵፭. ስለ ባለቤትነት

በጥብቅና ድርጅት ባለቤት መሆን የሚችሉት የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ጠበቆች ብቻ ናቸው::

፵፮. ስለ ጥብቅና ድርጅት መዋሐድና መከፋፈል

፩/ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የጥብቅና ድርጅቶች አግባብነት ባለው ሕግና የመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት መዋሐድ ይችላሉ፤ ውሕደቱ ሲፈፀም የነበረው የጥብቅና ድርጅት መብትና ግዴታ ወደ ተዋሐደው የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ይተላለፋል::

D) To perform other obligations under the partnership agreement, stipulated in this Proclamation and other relevant laws or arising from nature of the firm.

43. Distribution of Profits and Losses

Unless otherwise provided for in the partnership agreement of the law firm, members of the firm shall have the right to share in the profits and losses of the firm or in event of the liquidation of the partnership assets of the partnership in proportion to their shares in the firm.

44. Change of Members of the Firm

1/ Without prejudice to any prohibitions imposed by any other relevant law, a member who leaves the firm shall be paid the value of his share and his share of profit.

2/ Upon death of member of a law firm, the unpaid share of the profit due to the member shall be transferred to his legal heirs.

45. Ownership

Owner of a law firm shall only be advocates who have a valid advocacy license.

46. Merging and Division of Law Firms

1/ Two or more law firms may merge in accordance with relevant law and their bylaws; the rights and obligations of law firms that existed at the time of merging shall be transferred to the merged advocacy service firm.

፪/ የጥብቅና ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና አግባብነት ያለው ሕግ ከፈቀደ ድርጅቱ በሕግ መሠረት ሊከፋፈል ይችላል፤ የተከፋፈለው ድርጅት ቀድሞ የነበረው ድርጅት ላለበት መብትና ግዴታ እኩል ተጠያቂነት አለበት፤

፫/ የተዋሐዱና የተከፋፈሉ ድርጅቶች በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለባቸው፡፡

፵፯. የጥብቅና ድርጅት አስተዳደር

፩/ የጥብቅና ድርጅት በአባላት ውሳኔ በተሾሙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ባላቸው ሥራ አስኪያጆች ይተዳደራል፡፡

፪/ የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ አባላት መካከል የሚመረጥ መሆን አለበት፡፡

፫/ የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፡-

ሀ) ድርጅቱን በዋናነት ያስተዳድራል፤

ለ) ማንኛውንም ሕጋዊ የድርጅቱን መብት ለማስጠበቅና የድርጅቱን ግዴታ ለመወጣት የጥብቅና ድርጅቱን ይወክላል፤

ሐ) የድርጅቱ ተጠሪ ይሆናል፤

መ) ድርጅቱን ወክሎ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ይከራከራል፣ ጠበቃ ወይም ሦስተኛ ወገን ይወክላል፡፡

፬/ የጥብቅና ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሥራውን በሚያከናዉንበት ወቅት የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በሚፈፅመው ስህተት ምክንያት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ሥራ አስኪያጁ እና የጥብቅና ድርጅቱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

፭/ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት አድራሹ ሥራ አስኪያጅ ሥራዉን ለማከናወን ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን የሚያውቅ የነበረ ከሆነ የጥብቅና ድርጅቱ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

2/ If bylaw of the firm and relevant law permit, the organization may be divided in accordance with the law. The divided firm shall be equally liable for rights and obligations of the previous firm.

3/ Merged and divided firms shall be registered in accordance with this Proclamation.

47. Administration of Law Firm

1/ A law firm shall be managed by one or more managers appointed by the members.

2/ Manager of a law firm shall be elected from among members of the firm.

3/ Manager of the law firm shall:

A) Primarily manage the firm;

B) Represent the law firm in order to protect any legal rights of the firm and to fulfill obligations of the firm;

C) Be responsible for the firm;

D) Sue, be sued, argue, represent an attorney or third party on behalf of the organization.

4/ The manager of the law firm shall be jointly and severally liable for any damage caused to third parties due to an error committed by the manager of the law firm in the course of performing his duties with the intention of obtaining personal gain.

5/ The law firm shall not be liable if the injured party knew that the manager who caused the damage was not responsible for performing that duty.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ከተመለከተው ውጪ ከውል ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ለሚመጣ ግዴታ ኃላፊ የሚሆነው የጥብቅና ድርጅቱ ነው፡፡

፵፰. የሥራ አስኪያጅ ግዴታዎች

፩/ ሥራ አስኪያጁ በሽርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፡፡

፪/ የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ በውስጠ-ደንቦች፣ በሽርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሰው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ፡-

ሀ) አጠቃላይ የጥብቅና ድርጅቱን የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፤

ለ) በደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መቀበል እና መፍታት፤ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፤

ሐ) የድርጅቱን የሥራ ክንውን ሪፖርት የማዘጋጀትና ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤

መ) ድርጅቱን ኦዲት የማስደረግና መክፈል የሚጠበቅበትን ታክስ በታክስ ሕጉ መሠረት በወቅቱ የማሳወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፵፱. የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች

፩/ የጥብቅና ድርጅቱ በሽርክና ስምምነት ወይም ተፈጻሚነት ባለው ሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ቢያንስ ከግማሽ በላይ ድርሻ ያላቸዉ አባላቱ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

6/ The law firm shall be liable for any obligation arising out of or in connection with any contract or other circumstances other than those provided for in Sub-articles (4) and (5) of this Article.

48. Obligations of a Manager

1/ The manager shall fulfill the obligations imposed on him in accordance with the partnership agreement, this Proclamation and other relevant laws.

2/ The manager of the law firm shall ensure that the firm fulfills the obligations imposed on it in accordance with the by-laws, the partnership agreement, this Proclamation and other relevant laws.

3/ Without prejudice to the general provision of Sub-articles (1) and (2) of this Article, the manager shall have an obligation to:

A) Supervise the overall activities of the law firm in providing legal services;

B) Receive and solve complaints submitted by clients, and notify to relevant body when appropriate;

C) Prepare and submit a report on the performance of the firm to the relevant body;

D) Cause the firm to be audited and timely notify and pay the taxes due in accordance with the tax law.

49. Decisions of the Law Firm

1/ Without prejudice provided by the firm's partnership agreement or other applicable law, it shall be quorum when at least members who have more than half of the share attend the meeting.

፪/ የጥብቅና ድርጅቱ ሽሪኮች በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች የሚጸድቁት ስብሰባ ላይ ከተገኙት ሽሪኮች ቢያንስ 60% ድርሻ ያላቸዉን ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው፤

፫/ የጥብቅና ድርጅቱ አባላት በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የማኀበሩን መመሥረቻ ጽሑፍ ለማሻሻል ስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት የ2/3 (ሁለት ሶስተኛ) ይሁንታ ድምጽ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፶. ግብር

ማንኛዉም የጥብቅና ድርጅት ወይም ሽሪክ የግብር አከፋፈል አግባብነት ባላቸዉ የሽርክና ማኀበርን የተመለከቱ የግብር ሕጎች የሚወሰን ይሆናል፡፡

፶፩. ህልዉና እና መፍረስ

፩/ የጥብቅና ድርጅት ህልውና በሽሪኮቹ ሞት፣ መልቀቅ፣ ችሎታ ማጣት ወይም ሽሪኮቹን በሚያውክ ማናቸውም ለውጥ አይፈርስም፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ) የሽርክና ማኀበሩን ለማፍረስ አባላት ሲስማሙ፤

ለ) የጥብቅና ድርጅቱ መክሰሩ በፍርድ ቤት ሲታወጅ፤

ሐ) የሁሉም ሽሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ሲሰረዝ፣ ወይም

መ) የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ሽሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ሲልና ቁጥራቸው በጎደለ በስድስት ወራት ውስጥ የጸና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸዉ ሽሪኮቹ ቁጥር ቢያንስ ወደ ሁለት ካላደገ፡፡

2/ Without prejudice to the partners of the law firm agree otherwise, decisions of the law firm shall be adopted when they receive support of at least 60% of votes of the partners present at the meeting.

3/ Without prejudice to members of the law firm agree otherwise, amendment of memorandom of association shall require the approval of 2/3 (two-thirds) of the members present at the meeting.

50. Tax

The tax liability of any law firm or partnership shall be determined by the tax laws applicable to the partnership.

51. Existence and Dissolution

1/ Existence of a law firm shall not be dissolved by death, resignation, incapacity or any other change affecting the partners.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-article (1) of this Article, a law firm may be dissolved for one of the following reasons:

A) When members agree to dissolve the partnership;

B) When bankruptcy of the law firm is declared by court;

C) When advocacy license of all partners is revoked, or

D) When the number of partners with valid advocacy licenses is reduced to one and if the number of partners with valid law licenses is not increased to at least two within six months since their number is deteriorated.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) ድንጋጌ ቢኖርም የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በጥብቅና ድርጅቱ የቀረዉ ሽሪክ ለቢሮው ጥያቄ ሲያቀርብ እና ቦርዱ ጥያቄዉን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የስድስት ወራቱ የጊዜ ገደብ በሦስት ወራት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተደነገገዉ መሠረት ካልሆነ በስተቀር የሽሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ያለ መሆኑን የሚያዉቅ ሽሪክ የጥብቅና ድርጅቱ በዚህ ሁኔታ ከስድስት ወራት በላይ ሥራዉን እንዲቀጥል ካደረገ ለድርጅቱ እዳ እና ግዴታዎች ከጥብቅና ድርጅቱ ጋር በአንድነት እና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

፭/ የጥብቅና ድርጅት ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰረዛል፡፡

፮/ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማኅበርን መፍረስ የሚመለከቱ በንግድ ሕጉ ወይም በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች የጥብቅና ድርጅት መፍረስን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፶፪. የጥብቅና ድርጅት እና አባላት ኃላፊነት

በድርጅቱ አባላት ስምምነት ከተፈቀደው ውጭ በያዙት ጉዳይ ላይ ያልተገባ ተግባር ካልፈፀሙ ወይም ሥራቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም በማታለል ወይም አውቀው ባደረሱት ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ከጥብቅና አገልግሎት መስጠት ጋር በተያያዘ በጠበቆችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች አማካኝነት በደንበኞች እና ሌላ ሦስተኛ ወገን ላይ የሚደርስ ጉዳት በጥብቅና ድርጅቱ የደረሰ ጉዳት እንደሆነ ተቆጥሮ ድርጅቱ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

3/ Notwithstanding the provision of Sub-article (2) (D) of this Article, if the remaining partner of the firm submits a request to the Bureau before the expiry of the six-month period and the Board finds the request necessary, the six-month period may be extended by three months.

4/ Without prejudice to the provision in Sub-article (3) of this Article, if a partner who knows the number of partners has been reduced to one does not make the law firm to continue its business in this condition for more than six months, he shall be jointly and severally liable with the law firm for the debts and obligations with the firm.

5/ When a law firm is dissolved, it shall be deleted from the register.

6/ Provisions of the Commercial Code or other laws regarding dissolution of a limited liability company shall be applied to the dissolution of a law firm.

52. Liability of Law Firm and Members

The firm shall be liable for any damage caused to clients and other third parties by advocates and support staff in connection with the provision of legal services unless they have acted improperly on the case other than permitted by the agreement of members of the firm or have failed to perform their duties properly or have caused damage by deception or by deliberate action.

፶፫. ገንዘብ ጠያቂዎች

፩/ የጥብቅና ድርጅቱ ገንዘብ ጠያቂዎች ከድርጅቱ ማናቸውም ሀብት ላይ ገንዘብ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

፪/ በድርጅቱ አባላት ስምምነት ከተፈቀደው ውጭ በያዙት ጉዳይ ላይ ያልተገባ ተግባር ካልፈፀሙ ወይም ሥራቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም በማታለል ወይም አውቀው ባደረሱት ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ከጥብቅና ድርጅቱ ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ከድርጅቱ አባላት የግል ንብረት ላይ ገንዘብ መጠየቅ አይችሉም፡፡

፶፬. የጥብቅና ድርጅት ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ እና በንግድ ሕጉ ስለ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር የተቀመጡት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

፩/ ከሽሪኮቹ የሙያ ኃላፊነት መድን በተጨማሪ የጸና የሙያ ኃላፊነት መድን መግዛትና ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ይዞ መገኘት፤

፪/ ተገቢውን የሒሳብ ሰነድ መያዝ፤

፫/ የደንበኞቹን ምሥጢር መጠበቅ፤

፬/ በውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ኦዲት መደረግ፤

፭/ ይህንን አዋጅ፣ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕጎችና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንቦችን ማክበር፣ እና

፮/ በሽርክና ስምምነቱ ላይ ማሻሻያዎችን ሲያደርግ ማሻሻያው በተፈረመ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቢሮው ግልባጩን የማቅረብ፡፡

፶፭. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

፩/ ማንኛዉም የጥብቅና ድርጅት አባል ከድርጅቱ ስለ ሚወጣበት ሁኔታ እና የወጣ አባልን ድርሻ በተመለከተ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበርን የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

53. Claimants

1/ The claimants of the law firm may claim money from any of the firm's assets.

2/ Unless they have committed an improper act on the case they are handling or have not performed their duties properly or have caused fraud or damage knowingly other than permitted by partnership agreement of the firm, persons may not claim money from the personal assets of membrs of the firm.

54. Obligations of Law Firm

Without prejudice to obligations of a limited liability partnership in this Proclamation and the Commercial Code, a law firm shall have the following obligations:

1/ In addition to professional liability insurance of partners, to purchase and maintain professional indeminity insurance at all times while carrying out its business;

2/ To maintain proper accounting records;

3/ To maintain confidentiality of the clients;

4/ To be audited annually by an external auditor;

5/ To comply with this Proclamation, other relevant laws and professional ethics, and

6/ To submit copy of any amendment of partnership agreement to the Bureau within 30 consecutive days since the date of signing the amendment.

55. Applicability of Other Laws

1/ Relevant provisions of the Commercial Law relating to limited liability partnerships shall be applicable to circumstances in which any member of a law firm leaves the firm and shares of the member who has left.

፪/ በዚህ አዋጅ ከሚመራው ጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ተፈጥሮ ጋር የማይቃረኑ እስከሆነ ድረስ የንግድ ሕጉ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ በሚቋቋም የጥብቅና ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

ክፍል አምስት
የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር
ንዑስ ክፍል አንድ
የክልሉ ጠበቆች ማኅበር

፶፮. መቋቋም

፩/ የአማራ ክልል ጠበቆች ማኅበር ከዚህ በኋላ “ማኅበሩ” እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ማኅበሩ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት አለው፡፡

፫/ ማኅበሩ ሁሉንም ፈቃድ የተሰጣቸው የክልሉ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በአባልነት ያቀፈ ነው፡፡

፬/ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፈቃድ ሲሰጠው ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ የማኅበሩ አባል ይሆናል፡፡

፶፯. ዋና መሥሪያ ቤት

የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ባሕር ዳር ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ የተለያዩ ቦታዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች ሊከፍት ይችላል፡፡

፶፰. የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስለ መጥራት

፩/ ቢሮው ይህ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የማኅበሩን የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይጠራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተጠራው ጠቅላላ ጉባኤ የማኅበሩን አመራር አካላት ይሰይማል፡፡

2/ The Commercial Law and other relevant laws shall be applicable to law firms to be established by this Proclamation unless they are inconsistent with the nature of the law firm governed by this Proclamation.

PART FIVE
ADMINISTRATION OF LEGAL SERVICES
Sub-Part One
Bar Association of the Region

56. Establishment

1/ The Amhara Region Bar Association, hereinafter called as “the Association,” body is hereby established by this proclamation:

2/ The Association shall have its own legal personality;

3/ The Association shall consist of all licensed advocates and law firms of the region.

4/ Any advocate or law firm shall become member of the Association without any preconditions upon being granted a license to practice law.

57. Head Office

Headquarter of the Association shall be in Bahir Dar and it may open branch offices in various places in the region as necessary.

58. Calling of the First General Assembly

1/ The Bureau shall call the first general assembly of the Association within six months since the date of coming into force of this Proclamation.

2/ The general assembly called pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall appoint management bodies of the Association.

፫/ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በቀጣይ ስድስት ወር ውስጥ ሁለተኛውን ጉባኤ የሚያካሂድ ሲሆን በጉባኤውም የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማጽደቅ አለበት፡፡

፶፱. ስለ በጀት

የማኅበሩ ዋነኛ የገቢ ምንጭ፦

፩/ ከአባላቱ የሚሰበሰብ መዋጮ፤

፪/ ማኅበሩ ከሌሎች ሕጋዊ ምንጮች የሚያገኛቸዉ ገቢዎች ናቸው፡፡

፷. የማኅበሩ አቋም

፩/ ማኅበሩ የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ፤

ለ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤

ሐ) ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት፤

መ) ዋና ፀሐፊ፡፡

፪/ ማኅበሩ እንደ አስፈላጊነቱ ሥራዉን ለማከናወን ኮሚቴዎች ወይም በስሩ የሚሠሩ የሥራ ክፍሎች ሊያደራጅ ይችላል፡፡

፷፩. የማኅበሩ ሥልጣን እና ተግባራት

ማኅበሩ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የሕግ ሥልጠናን በበላይነት ይመራል፣ የሕግ ሥልጠናን የሚመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች ያስፈጽማል፤

፪/ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎችን እውቅና ይሰጣል፤

፫/ ይህንን አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በሚጥሱ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

፬/ ከሕግ ሥልጠና ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ክፍያዎችን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል ያስፈጽማል፤

3/ The general assembly of the Association shall hold its second assembly within the next six months and shall approve Bylaw of the Association in the assembly.

59. Budget

Main source of income of the association shall be from:

1/ Contributions collected from its members;

2/ Revenues the association receive from other legal sources.

60. Structure of the Association

1/ The association shall have the following management bodies:

A) General Assembly;

B) Executive Committee;

C) President and Vice President;

D) Secretary General.

2/ The association may organize committees or working groups under it to carry out its work as necessary.

61. Powers and Duties of the Association

The Association shall have the following powers and duties:

1/ Leads on top of legal training and enforce provisions of the Proclamation relating to legal training;

2/ Accredits legal training providers;

3/ Takes appropriate action against legal training providers who violate this Proclamation and other relevant laws;

4/ Issues and enforces directives regarding fees payable in connection with legal training;

፭/ የማኅበሩ አባላት ይህን አዋጅና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች እና መመሪያዎችን በማክበር የጥብቅና አገልግሎትን እየሰጡ መሆኑን ይከታተላል፤ የዲስፕሊን ተጠያቂነት የሚያስከትል ጥፋት ሲኖር ጥቆማ ለቢሮው ያቀርባል፤

፮/ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚገኝ የደንበኛ አደራ ሒሳብ አያያዝ እና ከአደራ ሒሳብ የሚገኝ ወለድን እና ማናቸውን ገቢን አጠቃቀም የሚመለከቱ መመሪያዎች ያወጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፯/ የማኅበረሰብ የንቃተ ሕግ ትምህርቶችን ይሰጣል፤

፰/ የደንበኞች ጥቅም መጠበቁን ያረጋግጣል እንዲሁም የደንበኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ ጠቀሜታ ያላቸው የጠበቃ መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፤

፱/ የጥብቅና አገልግሎት ሙያ እንዲያድግ፣ የሕግ ትምህርት ጥራት እንዲጠበቅ፣ የሕግ የበላይነት እንዲከበር እና ሰብዓዊ መብት እንዲከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል፤

፲/ የጥብቅና አገልግሎትን የሙያ ብቃት እና የሥነ-ምግባር ሁኔታ በተመለከተ የሕግ ጥናት በማድረግ የጥናት ውጤቱን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፷፪. የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጣቸውን ጠበቆች ከየዞን /የብሔረሰብ አስተዳደሮች/ በምርጫ የተወከሉ አስር አስር ተወካዮች የሚያካትት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የማኅበሩን ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፣ ይሽራል፤

5/ Monitors whether members of the Association are providing advocacy services in compliance with this Proclamation and other relevant laws and directives; submits a recommendation to the Bureau in case of any violation that may result in disciplinary liability;

6/ Issues directives regarding the management of client trust accounts held by advocates or law firms and the use of interest and any income from trust accounts; monitors its implementation;

7/ Provides community awareness training;

8/ Ensures whether interests of clients are protected, as well as monitors observance of rights of advocates essential to protecting interests of clients;

9/ Contributes its part to the development of advocacy service profession, maintenance of the quality of legal education, respect for the rule of law and respect for human rights;

10/ Conducts legal research regarding the professional competence and ethical status of the advocacy service, and implements results of the research; presents them to the concerned body, and monitors its implementation.

62. Powers and Duties of the General Assembly

The General Assembly consisting of ten representatives elected from each zone /nationality administrations/ licensed advocates in accordance with this Proclamation shall have the following powers and duties:

1/ Appoints and dismisses the President, Vice President and members of Executive Committee of the Association;

፪/ የማኅበሩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤

፫/ የአባላትን የመዋጮ መጠን እና የአከፋፈል ሥርዓት ይወስናል፤

፬/ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን እና የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፤

፭/ ለአባላቱ ጠቅላላ ጥቅም እና ለፍትሕ ተደራሽነት ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤

፮/ የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፤

፯/ በሌሎች የማኅበሩ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎች ከሕዝብ ጥቅም እና ከማኅበሩ ዓላማ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፰/ የተከታታይ የሕግ ሥልጠና የሚሰጡ የሥልጠና ርዕሶች፣ የተከታታይ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎች የእውቅና አሰጣጥ፣ ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ክፍያዎች እና አጠቃላይ የተከታታይ የሕግ ሥልጠና አመራርን የተመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፱/ የአደራ ሒሳብ አፈጻጸምን፣ ከአደራ ሒሳብ የሚገኝ ወለድና ማናቸውም ገቢ አጠቃቀም፣ የአደራ ሒሳብ አያያዝና አመራር የተመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲/ ለማኅበሩ በግልጽ ባልተሰጡ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤

፲፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣኑን በከፊል ለሌላ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፲፪/ የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ ያፀድቃል፡፡

፷፫. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቋም

፩/ ማኅበሩ የአስፈፃሚነት ሥልጣን ያለው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

2/ Approves the strategic plan, annual plan and budget of the Association;

3/ Determines the amount of membership fee and the system of payment;

4/ Examines and approves reports of the Executive Committee and external auditors;

5/ Decides on matters of importance to the general interest of the members and access to justice;

6/ Appoints external auditors;

7/ Ensures whether decisions made by other bodies of the Association are in line with the public interest and objectives of the Association;

8/ Issues directives regarding the topics of training courses offered by continuous legal training, accreditation of continuous legal training providers, fees payable in connection with the training and general management of continuous legal training; monitors its implementation;

9/ Issues directives regarding performance of trust account, use of interest and any income from trust account, management and administration of trust account; monitors its performance;

10/ Decides on matters not expressly given to the association;

11/ It may delegate its powers to another body in part if necessary;

12/ Issues, amends, and approves bylaw of the association.

63. Structure of the Executive Committee

1/ The Association shall have an Executive Committee with executive powers.

፪/ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰባት አባላት ይኖሩታል፡፡

፫/ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል ተመርጠው ይሾማሉ፡፡

፬/ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከመካከላቸው ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣሉ፡፡

፷፬. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ማኅበሩን ያስተዳድራል፤

፪/ የማኅበሩን ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል፤ ሰብሳቢው ጉባዔውን ይመራል፤

፫/ የጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

፬/ የሠራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤

፭/ የሠራተኞችን ደመወዝና አበል ይወስናል፤

፮/ ፕሬዝዳንቱ እና ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፯/ የማኅበሩን መተዳደሪያ ረቂቅ ደንብ ወይም የዚሁ ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባኤው ያስጸድቃል፤

፰/ በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፷፭. የፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ፕሬዝዳንቱ አጠቃላይ የማኅበሩን ሥራ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤዉ እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዝዳንቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

2/ The Executive Committee shall have seven members.

3/ Members of the Executive Committee shall be elected and appointed from among members of the General Assembly.

4/ Members of the Executive Committee shall elect the Chairperson and Deputy Chairperson from among themselves.

64. Powers and Duties of the Executive Committee

The Executive Committee shall have the following powers and duties:

1/ Administers the Association;

2/ Calls for the Annual General Assembly of the Association; the Chairperson presides over the assembly;

3/ Implements and enforces decisions of the General Assembly;

4/ Issues rules of procedure for the employees;

5/ Determines salaries and allowances of the employees;

6/ Follows up and supervises proper performance of duties of the President and Vice President;

7/ Prepares draft rules of procedure for the Association or draft amendments thereto and gets approved them at the General Assembly;

8/ Performs other duties assigned by the General Assembly.

65. Powers and Duties of the President and Vice President

1/ The President shall direct the general affairs of the Association and shall be accountable to the General Assembly and the Executive Committee.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-article (1) of this Article, the President shall have the following powers and duties:

ሀ) የማኅበሩን ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀት እና የሥራ ክንውን ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤

ለ) ማኅበሩን ወክሎ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

ሐ) ማኅበሩ በሚከስበት፣ በሚከሰስበት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የሕግ ጉዳይ ማኅበሩን ወክሎ የሚቀርብ ጠበቃ ይወክላል፣ የማኅበሩን ጉዳይ ማስፈጸም እንዲችል የማኅበሩን ሠራተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን እንደአስፈላጊነቱ ይወክላል፤

መ) የማኅበሩን ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀት፣ የሥራ ክንውን እና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሠ) ለሥራ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ረቂቅ ያዘጋጃል፣ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) በማኅበሩ የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የማኅበሩን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሰ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማኅበሩን ሥራዎች ይሠራል፣ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት ማኅበሩን ይወክላል፤

ሸ) የጠቅላላ ጉባዔና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ቀ) በዋና ፀሐፊው ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

በ) በጠቅላላ ጉባኤውና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፫/ የማኅበሩ ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ፡-

ሀ) ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ሊሠራ በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

ለ) በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

A) Presents the annual plan, budget and performance of the Association to the General Assembly;

B) Sign contracts, sue and be sued on behalf of the Association;

C) Represents the Association in any legal action, lawsuit or other similar legal matter, and represent the Association's employees or third parties as necessary to carry out the Association's business;

D) Prepares annual plan, budget, performance and financial report of the Association and presents same to the Executive Committee.

E) Prepares draft instructions for work and implements them when approved by the Executive Committee;

F) Hires and manages employees of the Association in accordance with the Human Resources Management Directives of the Association;

G) Performs activities of the Association in accordance with directives given by the Executive Committee and represents the Association in its relations with third parties;

H) Follows up implementation of decisions of the General Assembly and the Executive Committee;

I) Investigates and decides on complaints submitted against decisions of the Secretary General;

J) Performs other duties assigned by the General Assembly and the Executive Committee.

3/ Vice President of the Association, being accountable to the President, he shall:

A) Acts as the President in his absence or incapacity;

B) Performs such other duties as may be assigned by the Executive Committee or the President.

፷፮. ዋና ፀሐፊ

፩/ ዋና ፀሐፊው በሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እና ለፕሬዝደንቱ ይሆናል፡፡

፪/ ዋና ፀሐፊው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤውና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ቃለ-ጉባዔዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

ሐ) ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በሌላ ሁኔታ እንዲፈፅም የመወሰን ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ፀሐፊው ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በመሆን የማኅበሩን የባንክ ሒሣብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤

መ) የማኅበሩን የንብረት አስተዳደር እና የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት በአግባቡ መዘርጋቱን እና የሒሳብ ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) የማኅበሩ ንብረትና ሒሳብ ተቀባይነት ባለው የሒሳብ ዘዴ መያዙን ያረጋግጣል፤

ረ) ሌሎች በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፷፯. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለማኅበሩ ልዩ ልዩ አካላት የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች መያዝ ይኖርበታል፡-

፩/ ስለ ጠቅላላ ጉባኤው እና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አመራር አካላት አደረጃጀት፣ ኃላፊነት፤

፪/ ስለ ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት እና ሌሎች ሠራተኞች የሥራ ድርሻ፤

66. Secretary General

1/ The Secretary General shall be appointed by the Executive Committee and shall be accountable to the Executive Committee and the President.

2/ The Secretary General shall have the following powers and duties:

A) Ensures that minutes of the General Assembly and the Executive Committee are properly kept and maintained;

B) Prepares agenda of the Executive Committee meetings in consultation with the President;

C) Without prejudice to the Executive Committee's authority to otherwise decide, the Secretary General, together with other employees, shall open and operate the bank accounts of the Association;

D) Ensures that the association's asset management and accounting system is properly established and accounting documents are properly maintained;

E) Ensures that the association's assets and accounts are maintained in accordance with accepted accounting methods;

F) Performs other duties assigned by the Executive Committee and the President.

67. Matters to be Determined by the Association's Bylaw

Without prejudice to provisions of this Proclamation, by laws of the Association shall contain the following detailed provisions regarding various organs of the Association:

1/ Structure of the general assembly and the executive committee; responsibilities;

2/ Duties of the president, vice president and other employees;

፫/ የምርጫና የማኅበሩ ልዩ ልዩ አካላት ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት፤

፬/ የማኅበሩ ልዩ ልዩ አካላት የሥራ ዘመን፣ እና

፭/ ሌሎች ለማኅበሩ በሕግ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ

፷፰. መቋቋም

፩/ በቢሮ ኃላፊው ሰብሳቢነት የሚመራ የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ከዚህ በኋላ “ቦርዱ” እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ቦርዱ በቢሮ ኃላፊው አቅራቢነት ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ በርዕሰ-መስተዳድሩ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከቢሮው ሁለት ዐቃብያነ-ሕግ ------------- አባላት፤

ለ) ከጠበቆች ማኅበር ሁለት -------------------- አባላት፤

ሐ) ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ዳኛ ----- አባል፤

መ) በክልሉ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤቶች መካከል አንድ የሕግ መምህር --------አባል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት እንዲሰየሙ የቀረቡ አባላት በሰላሳ ቀናት ውስጥ በርዕሰ-መስተዳድሩ ካልተሰየሙ እንደተሰየሙ ተቆጥሮ ሥራቸውን ይጀምራሉ፡፡

፬/ ከሰብሳቢው በስተቀር የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን አንድ አባል ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ ሊሰየም አይችልም፡፡

፭/ በቢሮው ውስጥ የጠበቆችን ጉዳይ የሚከታተለው የሥራ ክፍል ኃላፊ የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ያለ ድምጽ ያገለግላል፡፡

3/ Procedure for elections and meetings of various bodies of the association;

4/ Term of office of various bodies of the association; and

5/ Other matters related to powers and duties granted to the association by law.

SUB-PART TWO

ADVOCATES ADMINISTRATION BOARD

68. Establishment

1/ An Advacates’ Administrative Board, hereinafter referred as “the Board”, chaired by Head of the Bureau, is hereby established.

2/ The Board shall consist of members nominated by Head of Government through sssssubmission of Head of the Bureau from among the following entities:

A) Two prosecutors from the bureau --------- Members;

B) Two from the Bar Association ------------ Members;

C) One judge from the Regional Supreme Court region --- Member;

D) One law lecturer from one of law schools among universities in the Region -------------------- Member.

3/ If members proposed to be nominated in accordance with Sub-Article 2 of this Article are not nominated by Head of the Government within thirty days, they shall be deemed to have been nominated and shall commence their duties.

4/ The term of office of members of the Board, except for the Chairperson, shall be three years, and no member shall be appointed for more than two terms.

5/ Head of the department responsible for advocate’s affairs in the Bureau shall serve as Secretary of the Board without vote.

፷፱. የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባራት

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በቢሮው የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጥ ኃላፊነት ከተሰጠው ዘርፍ ጋር በመመካከር ለጥብቅና ፈቃድ ጠያቂዎች ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሊስተናገዱ የሚችሉበትን የሚያመቻች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ የአመልካቾችን ማስረጃዎች መርምሮ ለአመልካቾች ፈቃድ ይሰጣል፤ ወይም የማይሰጥበት ምክንያት ካለ ይህንኑ ይወስናል፤

፪/ የፈተናውን ሥነ-ሥርዓት፣ ጊዜና ቦታ በመወሰን የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና መውሰድ ለሚገባቸው አመልካቾች ይሰጣል፤

፫/ የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፣ ለማለፊያ የሚያበቃ ነጥብ ይወስናል፣ ዉጤቱን ከውሳኔ ሐሳብ ጋር ለቢሮ ኃላፊው ያቀርባል፤

፬/ አመልካቹ ለፍትሕ ሥራ አካሄድ የሚስማማ የሥነ-ምግባር ብቃት ያለዉ መሆኑን ለማረጋገጥ ማንኛዉንም ሰዉ መጠየቅ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ይችላል፤

፭/ በማኅበሩና በልዩ ልዩ አካላቱ የሚወሰዱ እርምጃዎችና ውሳኔዎች እንዲሁም በማኅበሩ በሚወጡ መመሪያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች ሕጋዊነት ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፤

፮/ በማኅበሩ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ ሲቀርብለት ቅሬታዎችን ተቀብሎ ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል፤

፯/ በዋና ዲሲፕሊን ጉባዔ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርብለትን ይግባኝ አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል።

69. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties:

1/ In consultation with the department responsible for granting license of the Bureau, it shall examine evidences of applicants at least four times a year and grant the license to the applicants, provided that it is possible to facilitate the processing of applicants for the license within shorter period; or, if there is a reason not to grant it, it shall decide the same;

2/ Determine the procedure, time and place of the examination and shall give to the applicants legible to take qualification examination of advocacy;

3/ Mark examination papers, determine passing score, and submit results to Head of the Bureau with recommendation;

4/ May question any person or examine evidence to ensure whether the applicant has the moral character to conduct the justice process;

5/ Monitor legality of actions and decisions taken by the Association and its various bodies as well as the directives and other similar documents issued by the Association;

6/ Receive and examine complaints and render decisions on appeals against decisions made by the Association;

7/ Examine and render decisions on appeals against decisions made by the General Disciplinary Assembly.

፸. ስለ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት እና በጀት

፩/ በቢሮው የጠበቆችን ጉዳይ የሚከታተለው የሥራ ክፍል የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

፪/ የቦርዱ አባላት የቦርዱን ሥራ በሚፈፅሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

፸፩. የቦርዱ አሠራር እና ውሳኔ

፩/ ቦርዱ የአባላቱን መደበኛ ሥራ በማይጎዳና የቦርዱን ሥራ በማያስተጓጉል መልኩ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፪/ ከቦርዱ አባላት ቢያንስ አምስቱ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔ የሚሰጠው በስብሰባዉ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል በሆነ ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ የቦርዱ ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

፬/ ቦርዱ የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚና ፈተና ኮሚቴ ያደራጃል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ ቦርዱ የራሱን የውስጥ አሠራር ሥርዓት በተመለከተ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሳይቃረን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፸፪. በቦርዱ ውሳኔ ላይ ስለ ሚቀርብ ይግባኝ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) እና አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፯) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ መሠረት በቦርዱ በሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔዉን ባወቀ በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

70. The Board's Office and Budget

1/ The department that handles advocates' affairs in the Bureau shall serve as office of the Board.

2/ The remuneration to be paid to members of the Board while performing their duties shall be implemented in accordance with relevant law.

71. Procedures and Decisions of the Board

1/ The Board shall establish procedures that do not affect the regular work of its members and do not disrupt the work of the Board.

2/ It shall be quorum when at least five of the Board members are present.

3/ The Board's decisions shall be made by majority vote of the members present at the meeting, however, in the event of a tie, the vote of the chairperson shall be taken as decision of the Board.

4/ The Board shall establish a committee for review and examination of advocacy license; the details shall be determined by a directive.

5/ The Board may determine its own internal procedures by a directive without contravening provisions of this Proclamation.

72. Appeal Against the Decision of the Board

Without prejudice to the provisions of Article 9, Sub-Article (2) (D) and Article 40, Sub-Article (7) of this Proclamation, a party aggrieved by the final decision of the Board under Article 69 of this Proclamation can submit an appeal to the Supreme Court of the Region within 30 consecutive days of becoming aware of the decision.

ንዑስ-ክፍል ሦሥት

የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባዔ መቋቋምና አወቃቀር

፸፫. ስለ መቋቋም

፩/ ተጠሪነቱ ለቦርዱ የሆነ የጠበቆች ዲሲፕሊን ዋና ጉባዔ ከዚህ በኋላ “ዋና ጉባዔ” እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ዞኖችና የብሔረ-ሰብ አስተዳደሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ጉባዔውና ለመምሪያው የሆኑ የጠበቆች አስተዳደር ንዑሳን ጉባዔዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

፫/ የዋናው ጉባዔም ሆነ የንዑሳን ጉባኤዎች አባላት ሆነው የሚሰየሙት ጠበቆች፣ ዳኞች እና ዐቃብያነ-ሕግ በሕግ ዕውቀታቸው፣ በሥራ ልምዳቸው፣ በከፍተኛ የሥራ አፈጻጸም ውጤታቸው፣ በታታሪነታቸው፣ በፍትሐዊነታቸውና በሥነ-ምግባራቸው መልካም ስም ያተረፉና በሥራ ባልደረቦቻቸው ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚታመንባቸው መሆን አለባቸው፡፡

፸፬. የዋና ጉባዔው አባላት አሰያየም

ዋና ጉባዔው በዚህ አዋጅ መሠረት የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ አባላት ያልሆኑ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ በቢሮ ኃላፊ የሚሰየም ሰብሳቢን ጨምሮ ከቢሮው ሁለት ዐቃብያነ-ሕግ------------------------አባላት፤

፪/ ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ዳኛ------- አባል፤

፫/ ከጠበቆች ማኅበር ሁለት ጠበቆች ---------አባላት፤

፬/ ከክልሉ የሕግ ኢንስቲቲዩት አንድ አሠልጣኝ ወይም ተመራማሪ--አባል፤

፭/ ከክልሉ ሴቶች ማኅበር ሊቀ-መንበር ወይም ተወካይ--አባል፤

SUB-PART THREE

ESTABLISHMENT AND STRUCTURE OF THE ADVOCATES' DISCIPLINARY COUNCIL

73. Establishment

1/ The Advocates' Disciplinary Main Council accountable to the Board, hereinafter called as “Main Council”, is established by this proclamation.

2/ The Advocates' Administration Sub-Councils which are accountable to the main council and to the Zonal Justice Department are established by this proclamation.

3/ The advocates, judges and prosecutors appointed as members of both the main council and the sub-councils must have a good reputation for their legal knowledge, work experience, high performance, diligence, fairness and ethics, and must be highly trusted by their colleagues.

74. Appointment of the Main Council Members

The Main Council shall, in accordance with this proclamation, consist of the following members who are not members of the Bar Association Administrative Board:

1/ Two prosecutors from the Bureau, including a chairperson to be nominated by head of the bureau ……………………………………………Members;

2/ One judge from Regional Supreme Court… Member;

3/ Two lawyers from the Bar Association,…Memebers;

4/ One trainer or researcher from the Regional Law Institute………………………………Members;

5/ Chairperson or representative of the Regional Women's Association……………………Member;

፮/ የአንድ አባል የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፤

፯/ የጉባዔው ፀሐፊ ከአባላቱ ውስጥ በጉባዔ አባላት ይመረጣል፡፡

፸፭. የጠበቆች ዲስፕሊን ዋና ጉባኤ ሥልጣን እና ተግባራት

ዋና ጉባኤው፡-

፩/ ይህንን አዋጅ በመተላለፍ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት ላይ የሚቀርብን ክስ ተቀብሎ ያጣራል፣ ይመረምራል፤

፪/ ክሱ እና ማስረጃው ጠበቃውን ወይም የጥብቅና ድርጅቱን የሚያስቀርብ መሆኑን ከወሰነ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ መልሱን በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ እንዲያቀርብ በመጥሪያ ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃው ይልካል፤

፫/ በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ላይ የቀረበውን ክስ እና ማስረጃ፣ በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ በኩል የተሰጠ መልስ እና ማስረጃ ከመረመረ እና ካከራከረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፤

፬/ በንዑስ-ጉባዔ በተሰጠ ውሳኔ በቀረበ ቅሬታ ላይ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭/ የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሥራ አፈጻጸም ከሙያ ሥነ-ምግባር ደንቡ ጋር የተጣጣመ መሆኑን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፮/ ለጠበቆች ሥነ-ምግባር ግድፈት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችን እያጠና በሚያገኘው ግብዓት መሠረት ማኀበሩ የበኩሉን እርምጃ እንዲወስድ ውጤቱን ይልክለታል፤ ለቢሮውም ያሳውቃል፡፡

6/ The term of office of a member is two years and he cannot be elected more than twice;

7/ Secretary of the council shall be elected from among the members by the council members.

75. Powers and Duties of the Advocates' Discipline Main Council

The Main Council:

1/ Receives and investigates any complaint filed against an advocate or law firm in violation of this Proclamation;

2/ If it determines that the complaint and evidence make the advocate or law firm bring near, it shall send the complaint to the advocate or law firm stating in a summon that they must submit a response in writing within 30 consecutive days;

3/ Renders a decision after examining and arguing the charges and evidence against the advocate or law firm, and the answers and evidence provided by the advocate or law firm;

4/ Investigates and renders decision on a complaint submitted against a decision made by sub-council;

5/ Establishes a system to monitor whether the work performance of advocates and law firms is in accordance with the code of professional ethics;

6/ Sends results of its investigation into causes of misconduct by advocates, based on the information it receives, to the Bar Association for it to take appropriate action, and shall inform same to the bureau.

፸፮. ስለ ንዑሥ ጉባዔ አባላት አሰያየም

በዚህ አዋጅ መሠረት ንዑሥ ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ በመምሪያ ኃላፊው የሚሰየም አንድ ሰብሳቢን ጨምሮ ከመምሪያው ሦስት ዐቃብያነ-ሕግ፤

፪/ ከዞኑ /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ዳኛ-----------------------------------አባል፤

፫/ ከዞኑ /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ የጠበቆች ማኅበር ሁለት ጠበቆች------------------------------አባላት፤

፬/ የዞኑ የሴቶች ማኅበር ሊቀ-መንበር ወይም ተወካይ------------------------------------አባል፡፡

፸፯. የንዑሥ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባራት

የንዑስ ጉባዔ ተጠሪነት ለዋና ጉባዔዉ እና ለሚገኝበት መምሪያ ሆኖ፡-

፩/ ጠበቆችን ወይም የጥብቅና ድርጅቶችን በተመለከተ ቀላል የዲሲፕሊን ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል፤

፪/ በዞኑ እና በስሩ በሚገኙ ወረዳዎች በሚሠሩ ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች የሚፈጸሙ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በመመርመር ውጤቱን ለመጨረሻ ውሳኔ ለዋናው ጉባዔ ያስተላልፋል፤

፫/ በዋናው ጉባዔ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፸፰. የጉባዔዎች የስብሰባ ጊዜና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት

የእያንዳንዱ ጉባኤ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ ጉባዔዎቹ ቢያንስ በየሦስት ወሩ የየራሳቸውን ስብሰባ ያደርጋሉ፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የየጉባኤዎቹ ሰብሳቢዎች ስብሰባ ሊጠሩ ይችላሉ፤

76. Appointment of the Sub-committee Members

According to this proclamation, the sub-committee shall have the following members:

1/ Three prosecutors from the department, including the chairperson to be appointed by head of the department;

2/ One judge from high court of the zone /national administration/ ------------------------------Member;

3/ Two advocates from the bar association of the zone /national administration/ -----------------Member;

4/ Chairperson or representative of women's association of the zone----------------------------------Member.

77. Powers and Duties of Sub-assembly

The Sub-Assembly shall be accountable to the General Assembly and the Department to which it is located and:

1/ Investigates and decides on minor disciplinary matters concerning advocates or law firms;

2/ Investigates serious disciplinary offenses committed by advoctaes or law firms working in the zone and its subordinate districts and submit results to the General Assembly for final decision;

3/ Performs other related duties assigned by the General Assembly.

78. Meeting Times and Procedures of the Assemblies

Procedure of each assembly shall be as follows:

1/ Assemblies shall hold their respective meetings at least every three months;

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, chairmen of each assembly may call a meeting whenever it is necessary to convene an extraordinary meeting;

፫/ በማናቸውም ስብሰባ ከአባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤
፬/ ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት ያብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤
፭/ የጉባዔዎቹ አባላት ድምጾች እኩል የተከፈሉ እንደሆነ ሰብሳቢዎቹ ወሳኝ ድምጽ ይኖራቸዋል፤
፮/ ጉባዔዎቹ ጉዳዮችን በአብላጫ ድምጽ በሚወስኑበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየቶች በስብሰባዎቹ ቃለ-ጉባዔዎች መመዝገብ ይኖርባቸዋል፤
፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፮) የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔዎቹ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የራሳቸውን ዝርዝር ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸሚያ ደንቦች ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

፸፱. ስለ ጉባዔ አባላት መብትና ግዴታዎች

የጉባዔ አባላት ከዚህ የሚከተሉት መብትና ግዴታዎች ይኖሯቸዋል፡-
፩/ በጉባዔው ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤
፪/ በመደበኛና በአስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት፤
፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያሳልፉት ውሳኔም ሆነ ለሚፈጽሙት ማናቸውም ተግባር የግልና የጋራ ኃላፊነት የመውሰድ፡

ንዑስ ክፍል አራት
ስለ ቢሮው

፹. የቢሮው ተግባር

ቢሮው፡-
፩/ በቦርዱ ውሳኔ መሠረት የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ለወሰነለት ባለሙያ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፤
፪/ ጠበቆችን፣ የጥብቅና ድርጅቶችን እና ከጠበቃ እና ጥብቅና ድርጅቶች ጋር የሚሠሩ ሰዎችን ይመዘግባል፣ የጥብቅና ፍቃድ ያድሳል፤

3/ It shall be quorum at any meeting when more than half of the members are present;
4/ Any matter shall be decided by majority vote of the members present at the meeting;
5/ In the event of tie of votes among members of the assemblies, the chairperson shall have a casting vote;
6/ Whenever assemblies decide matters by majority vote, opinions of the minority shall be recorded in the minutes of meetings;
7/ Without prejudice to the provisions from Sub-articles (1) to (6) of this Article, assemblies may, when they deem necessary, issue their own detailed rules of procedure.

79. Rights and Obligations of Assembly Members

Members of the Assembly shall have the following rights and obligations:
1/ To participate in the meetings of the Assembly;
2/ To attend regular and extraordinary meetings;
3/ To take personal and collective responsibility for the decisions they make and for any actions they take in accordance with this Proclamation.

SUB-PART FOUR
THE BUREAU

80. Duties of the Bureau

The bureau shall:
1/ Grant advocacy license to a professional who has been determined to be given advocacy license in accordance with the Board's decision;
2/ Register advocates, law firms and persons working with law firms, and renew their licenses;

፫/ በዲስፕሊን ጉባዔ የውሳኔ ሐሳብ መነሻነት ቦርዱ በሚወስነው መሠረት የጥብቅና ፈቃድ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፬/ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው መሠረት ለሚሰጠው የጥብቅና ፈቃድና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ ይሰበስባል፤

፭/ ከማኅበሩ ጋር በመመካከር በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ለሚሰጡ የሕግ አገልግሎቶች መለኪያዎችን ያወጣል፤

፮/ የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ ጥቆማ በቀረበበት ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ላይ የሥነ-ምግባር ጥሰቱ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ምርመራ ያካሂዳል፣ የዲስፕሊን ክስ ይመሠርታል፤ ይከራከራል፤

፯/ የጠበቃንና የጥብቅና ድርጅትን መረጃ የሚይዝና ለሕዝብ ክፍት የሆነ መዝገብ ያደራጃል፤

፰/ በጠበቃና የጥብቅና ድርጅት ላይ በየጊዜው የተጣሉና የሚጣሉ ቅጣቶችን ይመዘግባል፣ ያስፈጽማል፤ ከየግል ማህደሮቻቸው ጋር እንዲያያዙ ያደርጋል፤

፱/ የጠበቃና የጥብቅና ድርጅት ብቃትና ሥነ-ምግባር የሚጎለብትባቸውንና የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅባቸውን ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፤

፲/ ማኅበሩ እንዲጠናከር ለማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፲፩/ ማኅበሩ ከሌሎች ተቋማት ጋር ሕጋዊ ግንኙነት ስለሚፈጥርበት ሁኔታ የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፪/ የፌደራል ጥብቅና ፈቃድ አውጥተው በክልሉ ፍርድ ቤቶች ወይም በሌሎች አካላት ፊት ቀርበው የጥብቅና ሥራ የሚሠሩ ጠበቆች በደንበኞች ላይ ሕገወጥ ተግባር መፈጸማቸውን ሲያረጋግጥ ፈቃድ ላወጡበት አካል ሪፖርት ያደርጋል፤ በሕግ የሚጠየቁበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

3/ Suspend or revoke license of advocacy as determined by the Board based on decision of the Disciplinary Council;

4/ Collect fees from license and other services provided in accordance with the directive to be issued pursuant to this Proclamation;

5/ Establish standards for legal services provided by advocates and law firms in consultation with the Association;

6/ Conduct investigation on any alleged violation of ethics by any advocate or law firm to determine whether the violation has been occurred, initiate disciplinary proceedings, and litigate;

7/ Maintain a public record of information about advocates and law firms;

8/ Record and enforces penalties imposed and to be imposed on advocates and law firms from time to time; and ensure same are attached with their personal files;

9/ Create favorable conditions in which competence and ethics of advocates and law firms to be developed and dignity of advocacy profession to be maintained;

10/ Provide appropriate support and supervision for the establishment of various organizations to strengthen the association;

11/ Take its part in the establishment of legal relations between the association and other institutions;

12/ Report to the body that issued the license when it is confirmed that advocates who have obtained a federal advocacy license and appear before regional courts or other bodies and practise advocacy have committed illegal acts against clients; create an environment in which they can be held accountable by law;

፲፫/ የጥብቅና አገልግሎት የሚዳብርበትን ሁኔታ ከፌደራልና ከሌሎች ክልሎች ጋር በጋራ ይሠራል፤

፲፬/ ፈቃድ የተሰጠበትን ሀገር ሕግን በሚመለከት እና በዚህ አዋጅ መሠረት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ካገኘ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ጋር በመሆን በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ ያለው ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በያዘው የውጭ ሀገር ጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ በክልሉ ውስጥ ለደንበኞቹ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፤

፲፭/ ሌሎች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባራት ይፈጽማል።

ክፍል ስድስት
የዲሲፕሊን ጥፋቶች እና ቅጣት
ንዑስ ክፍል አንድ
ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት እና ቅጣት

፹፩. ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት አይነቶች

የሚከተሉት እና መሰል ጥፋቶች በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

፩/ የጥብቅና ፈቃድን ለደንበኛ፣ ለፍርድ ቤት ወይም ለሚመለከተው አካል እንዲያሳይ በተጠየቀ ጊዜ ለማሳየት ፈቃደኛ ያለመሆን፤

፪/ ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታ፣ የደረሰበትን ደረጃና የሚገኝበትን ሁኔታ በየጊዜው ለደንበኛው አለማሳወቅ፤ ደንበኛን ማመናጨቅ ወይም ክብሩን መንካት፤

13/ Work together with the federal and other regions to develop advocacy services;

14/ May allow license to be granted in accordance with law of a country in which the license is issued and this Proclamation being together with an advocate or law firm licensed to provide legal services in accordance with law of a foreign country to provide legal services to his clients within the region under the foreign law;

15/ Exercise such other powers and functions given to it based on this Proclamation and a regulation to be issued pursuant to this Proclamation and other relevant laws.

PART TWO
DISCIPLINARY OFFENSES AND PENALTY
SUB-PART ONE
MINOR DISCIPLINARY OFFENSES AND PENALTY

81. Types of Minor Disciplinary Offenses

The following and similar offenses are minor disciplinary offenses committed by an advocate or law firm:

1/ Refusal to show the advocacy license to a client, court or relevant body when requested to do so;

2/ Failure to inform the client regularly of the status, progress and status of the case; disrespect of a client or violation of his dignity;

፫/ ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት በሰዓቱ ያለመገኘት ወይም መዘግየት ወይም ያለበቂ ምክንያት ደንበኛን ብቻ ፍርድ ቤት በመላክ መቅረት፤

፬/ ለጠበቆች ማኅበር መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያ ወይም መዋጮ በወቅቱ ያለመክፈል፤

፭/ ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቢሮው ወይም በማኅበሩ በሚጠራ የምክክር መድረክ ላይ ያለመገኘት፤

፮/ በፍርድ ቤት ወይም መሰል ተቋማት የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር፤

፯/ ባልታደሰ የጥብቅና ፈቃድ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፡፡

፹፪. የቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተደነገጉ ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ብር 5,000 (አምስት ሺ.ህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩ ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፭) የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ ከብር 5,000-7,000 (አምስት ሺ.ህ እስከ ብር ሰባት ሺ.ህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩ ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) የተደነገገዉን ጥፋት የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ ከብር 5,000 (አምስት ሺ.ህ) እስከ ብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ Failure to appear in court on time or late on the appointed day without sufficient and convincing reason or to send a client to court alone without sufficient reason;

4/ Failure to pay the fee or contribution required to be paid to the Bar Association on time;

5/ Failure to attend a meeting convened by the Bureau or the association without sufficient and convincing reason;

6/ Slandering, defaming or otherwise attempting to diminish dignity of a professional colleague in court or similar institutions;

7/ Rendering advocacy service without renewing the advocacy license.

82. Penalty for Minor Disciplinary Offenses

1/ An advocate or law firm that commits any of the offenses provided under Article 81, Sub-articles (1) and (2) of this Proclamatin shall be punished with a fine up to Birr 5,000 (Five Thousand), as the case may be.

2/ An advocate or law firm that commits any of the offenses provided under Article 81, Sub-articles (3) to (5) of this Proclamation shall be punished a fine from Birr 5,000-7,000 (Five Thousand to Seven Thousand), as the case may be.

3/ An advocate or law firm that commits offenses stipulated in Article 81, Sub-Articles (6) and (7) of this Proclamation shall be punished with a fine ranging from Birr 5,000 (Five Thousand) to Birr 10,000 (Ten Thousand), as the case may be.

ንዑስ ክፍል ሁለት

ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት እና ቅጣት

፹፫. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ዓይነቶች

የሚከተሉት እና መሰል ጥፋቶች በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ስር የተዘረዘሩ ሰዎችን በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት መቅጠር እና ማሠራት፤

፪/ በስሩ የቀጠራቸውን የሕግ ጉዳይ ፀሐፊዎች፣ የጠበቃ ረዳትና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ለፈቃድ ሰጭው አካል ያለማሳወቅና ያለማስመዝገብ፤

፫/ ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት ተለዋጭ ቀጠሮ በተደጋጋሚ መጠየቅ ወይም ጉዳዩ እንዲጓተት ማድረግ፤

፬/ የጥብቅና አገልግሎት መስጫ ቢሮ ሳይኖር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

፭/ በሕግ ከተፈቀደው ምክንያት ውጭ የሕግ ሥልጠና በአግባቡ አለመውሰድ፤

፮/ በሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር የደንበኛን ምስጢር አለመጠበቅ፤

፯/ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተዉ አካል ሲመራለት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፤

፰/ የጥብቅና ሥራን በአገናኝ አማካኝነት መሥራት ወይም ለሌላ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የድለላ ወይም የአገናኝነት ሥራ መሥራት፤

፱/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ከተደነገገዉ በስተቀር ስለአገልግሎት ዓይነቱ፣ የአገልግሎት ክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሥርዓት፣ የጠበቃ/የጥብቅና ድርጅቱ ግዴታ፣ የደንበኛው ግዴታንና ሌሎች እንደጉዳዩ ዓይነት አስፈላጊ ነጥቦችን ያልያዘ የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነትን በጽሑፍ ያለማድረግ፤

SUB-PART TWO

SERIOUS DISCIPLINARY OFFENCES AND PENALTY

83. Types of Serious Disciplinary Offences

The following and similar offences committed by an advocacy or law firm are serious disciplinary offences:

1/ Employing and cause working persons listed under Article 17, Sub-Article (3) of this Proclamation as legal clerks;

2/ Failing to notify and get registered the legal clerks, legal assistants and support staff employed by him to the licensing body;

3/ Repeatedly requesting alternative appointments without sufficient and convincing reason or delaying the case;

4/ Providing legal services without a legal service office;

5/ Failure to properly undertake legal training except for reasons permitted by law;

6/ Failure to maintain clients' confidentiality unless permitted by law;

7/ Refusal to accept a request from a relevant body to provide free legal services;

8/ Performing advocacy work through an intermediary or acting as a broker or intermediary for another advocate or law firm;

9/ Failing to conclude a written agreement on the type of service, the amount of service fee and the payment system, obligations of the advocate/law firm, obligations of the client and other relevant points in the case, except as provided in Article 22, Sub-Article (2) of this Proclamation;

፲/ ያለበቂ ምክንያት የጥብቅና ውልን ማቋረጥ ወይም የጥብቅና ውልን በማቋረጥ ለደንበኛ በተገቢው ጊዜ አለማሳወቅ፤

፲፩/ ለተቀበለው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ አለመስጠት ወይም በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ ከደንበኛው አላግባብ ክፍያ መጠየቅ ወይም መቀበል፤

፲፪/ የጥብቅና ፈቃዱን ለቢሮው ሳይመልስ በቋሚ ሥራ ተሠማርቶ መገኘት፤

፲፫/ የጥቅም ግጭት የሚያስነሣ ወይም የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ መሆኑን እያወቀ ጉዳዩን መያዝ፤

፲፬/ ከተሰጠው የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በላይ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

፲፭/ ስለራሱ ወይም ስለድርጅቱ ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ሐሰተኛ የሆነ ወይም የሚያሳስት መግለጫ መስጠት፤

፲፮/ ከደንበኛው በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው የጥብቅና አገልግሎት የውክልና ሥልጣን ሳይሰጠው የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

፲፯/ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት አባል ሆኖ ሳለ በግል የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

፲፰/ የደንበኛውን ንብረት ወይም ሰነድ በአግባቡ አለመያዝ፤

፲፱/ ብቃት ያለው አገልግሎት ያለመስጠት ወይም የደንበኛን ማስረጃ በአግባቡ ለፍርድ ቤት ወይም መሰል የዳኝነት አካላት አለማቅረብ፤

፳/ የጥብቅና ፈቃድን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን መጠቀሚያ አሳልፎ መስጠት፤

፳፩/ ልዩ የጥብቅና ፍቃድ በመውሰድ በሚሰጠው አገልግሎት ደንበኛውን ክፍያ መጠየቅ፣

፳፪/ በነፃ እንዲያገለግል ለያዘው ጉዳይ ክፍያ ማስከፈል፤

10/ Terminating an advocacy contract without sufficient reason or failing to inform the client in proper time of terminating the advocacy contract;

11/ Failure to provide a receipt for the fee for legal services received or requesting or accepting improper payments from the client in addition to the fee for legal services specified in the legal services agreement;

12/ Being engaged in permanent work without returning the legal services license to the bureau;

13/ Handling a matter that raises conflict of interest or knowing that it has conflict of interest;

14/ Providing legal services beyond the level of legal services granted;

15/ Making false or misleading statements about himself or the firm or the services provided;

16/ Providing legal services without legally acceptable power of advocacy from the client;

17/ Providing legal services privately while being member of a legal services firm;

18/ Failure to properly handle his client's property or documents;

19/ Failure to provide competent services or to properly present the client's evidence to a court or similar judicial body;

20/ Transferring advocacy license to third party for use in any way;

21/ Requesting payment from client for the services provided by obtaining special advocacy license;

22/ Charging fee for a case that was supposed to be served free of charge;

፳፫/ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ለሚሰጠው ሰው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ግዴታውን በአግባቡ ባለመወጣት የደንበኛን ጉዳይ እንዲበላሽ ወይም ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

፳፬/ ከተቃራኒ ባለጉዳይ ጠበቃ ጋር በመመሳጠር ማስረጃ ማጥፋት ወይም የደንበኛ ጉዳይ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

፳፭/ የሕግ መሠረት የሌለውን እና እንደማያዋጣ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ያዋጣል በማለት መያዝ እና ከደንበኛ ክፍያ መቀበል፤

፳፮/ በዳኝነት ወይም በዓቃቤ ሕግነት ወይም በነገረ ፈጂነት በሚሠራበት ወቅት ያየውን ጉዳይ ወይም በሽምግልና ወይም በቀድሞ መሥሪያ ቤት በሚሠራበት ጊዜ ይዞት በነበረው ጉዳይ ላይ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ወይም ለመስጠት መሞከር፤

፳፯/ ሐሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም ወይም በማንኛውም ሁኔታ በማታለል የጥብቅና ፈቃድ ማውጣት፤

፳፰/ በእምነት ማጉደል፣ ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም መገልገል፣ ስርቆት እና በመሳሰሉት ከሥነ-ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤

፳፱/ ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ መምከር፤

፴/ ሐሰተኛ ምስክር በማዘጋጀት በሐሰት ማስመስከር፣ ተከሳሽ ወይም ምስክር ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ፤

፴፩/ ለተቃራኒ ወገን ጠቃሚ የሆነን ማስረጃ እንዳይጠቀምበት በማሰብ ማጥፋት ወይም እንዲጠፋ ደንበኛን መምከር፤

23/ Intentionally or negligently failing to properly fulfill his duty to a person providing free legal services, causing the client’s case to be damaged or ineffective;

24/ Collusion with an opposing advocate to destroy evidence or make a client’s case ineffective;

25/ Treating a case that is clearly unfounded and untenable as valid and accepting payment from a client;

26/ Providing or attempting to provide legal services in a case that he has seen while serving as a judge, prosecutor, or arbitrator, or in a case that he or she has handled in a mediation or other capacity while serving in a previous office;

27/ Obtaining advocacy license by using false evidence or by any means of deception;

28/ Being convicted in court of a crime involving breach of trust, deception, fraud, preparation or use of false document, theft and other crimes related to misconduct;

29/ Providing or advising for the provision of false evidence;

30/ Causing for false testimony preparing same, making defendant or witness fail to appear to court;

31/ Losing or advising to be lost of evidence useful to the opposing party with the intention of preventing it from being used;

፴፪/ ለፍትሕ አካላት ወይም ለተቃራኒ ተከራካሪ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለመስጠት ከደንበኛው ገንዘብ ወይም ንብረት በመቀበል መስጠት ወይም ለመስጠት መሞከር፤

፴፫/ በታገደ ወይም በተሰረዘ የጥብቅና ፈቃድ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት።

፹፬. የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፯) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር 10,000 (አስር ሺህ) እስከ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ ከንዑስ አንቀጽ (፰) እስከ (፲፯) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር 20,000 (ሃያ ሺህ እስከ ብር 50,000 (ሀምሳ ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ ከንዑስ አንቀጽ (፲፰) እስከ (፳፯) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ይታገዳል።

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ ከንዑስ አንቀጽ ፳፯ እስከ ፴፫ ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ይሰረዝበታል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ፈጽሞ በአምስት ዓመት ጊዜ ዉስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ስር የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆንበታል።

32/ Receiving or attempting to give money or property from the client to give to judicial bodies or opposing advocate or law firm;

33/ Providing legal services with a suspended or revoked advocacy license.

84. Penalty for Serious Disciplinary Offenses

1/ An advocate or law firm that commits any of the offenses listed from Sub-articles (1) to (7) of Article 83 of this Proclamation shall be punished a fine of Birr 10,000 (Ten Thousand) to Birr 20,000 (Twenty Thousand).

2/ An advocate or law firm taht commits any of the offenses listed from Sub-articles (8) to (17) of Article 83 of this Proclamation shall be punished a fine of Birr 20,000 Twenty thousand) to Birr 50,000 (Fifty Thousand).

3/ An advocate or law firm that commits any of the offenses listed in Article 83, from Sub-Articles (18) to (26) of this Proclamation, his license or registration certificate shall be suspended for a period of up to six months, as the case may be.

4/ An advocate or law firm that commits any of the offenses listed in Article 83, from Sub-Articles (27) to (33) of this Proclamation, his license or registration certificate shall be revoked.

5/ An advocate or law firm that has been convicted of any of the offenses listed in Sub-Articles (1) and (2) of this Article twice within a period of five years shall be subject to the provision of Sub-Article (3) of this Article if it commits another similar serious disciplinary offense.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ስር የተጠቀሰዉን ቅጣት ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

፯/ ቀላልም ሆነ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ የሚመለከተው የዲሲፕሊን ጉባዔ እያንዳንዱን ጥፋት መሠረት ያደረገ ቅጣት ይወስናል፡፡

፰/ በዲሲፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም፡፡

፹፭. ውሳኔን ስለ መከለስ

፩/ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ላይ የተወሰነው ቅጣት በሐሰተኛ ሰነድ ወይም የምስክርነት ቃል ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከተገኘ ጉባዔው ጉዳዩን እንደገና በመመርመር እንደተገቢነቱ ተለዋጭ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በጉዳዩ ላይ ድጋሜ ምርመራ ሊያካሂድ የሚችለው በሐሰት ማስረጃ ነጻ ተሰናብቶ ከሆነ አቤቱታ አቅራቢው ተቃራኒ ማስረጃ መገኘቱን ባወቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሲያቀርብ ይሆናል፤ ሆኖም ውሳኔው ከተሰጠ ከሁለት ዓመታት በኋላ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

ንዑስ ክፍል ሦስት

ስለ ዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ፣ ይርጋ፣ ይግባኝ እና የወንጀል ቅጣት

፹፮. ስለ ዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ይርጋ

፩/ የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ እና የክርክር ሥነ-ሥርዓት በመደበኛው የወንጀል ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሚመራ ይሆናል፡፡

6/ If an advocate or law firm that has been punished twice under Sub-article (3) of this Article is found guilty of another serious disciplinary offense, Sub-article (4) of this Article shall be applied on him.

7/ In the event that minor as well as serious disciplinary offenses are found to have occurred, the relevant disciplinary council shall determine the appropriate punishment for each offense.

8/ Being found guilty of a disciplinary offense and being punished shall not exclude criminal liability.

85. Review of Decision

1/ If the penalty imposed on an advocate or law firm is found to be based on false document or testimony, the Council may re-examine the matter and issue an alternative decision as appropriate.

2/ The Council may conduct the re-examination of a case under Sub-article (1) of this Article if the petitioner has been acquitted on false evidence, provided that he submits the petition within one month of learning that contrary evidence has been found; however, a petition submitted after two years from the date of the decision shall not be admissible.

SUB-PART THREE

Submission, Period of Limitation, Appeal and Criminal Penalty of Disciplinary Cases

86. Submission of Disciplinary Cases and Period of Limitation

1/ Submissdion of disciplinary cases and litigation procedure shall be governed by the standard of criminal procedure.

፪/ በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ መፈጸሙ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፫/ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ መፈጸሙ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠር የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፬/ ማንኛዉም የዲሲፕሊን ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ ቀላል ከሆነ ለሁለት ዓመት ከባድ ከሆነ ለሶስት ዓመት ሳይፈጸም ከቆየ አፈጻጸሙ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፹፯. ስለ ይግባኝ

፩/ በንዑስ ጉባዔ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ (30) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለዋና የዲሲፕሊን ጉባዔ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዋናው ጉባዔ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ (30) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡

፹፰. የወንጀል ቅጣት

በዚህ አዋጅ በወንጀል የሚያስቀጡ ጥፋቶችን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

ንዑስ ክፍል አራት

ስለ መሰየም

፹፱. የመሰየም አቤቱታ አቀራረብ

፩/ ይህንን አዋጅና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኛነት ሪከርድ እንዲሰረዝለትና ስሙ እንዲመለስለት መጠየቅ ይችላል፡፡

2/ A case filed for minor disciplinary offense shall be suspended by period of limitation if it is not filed within one year from the date on which the disciplinary offense was discovered.

3/ A case filed against serious disciplinary offense shall be suspended by period of limitation if it is not filed within two years from the date on which the disciplinary offense was discovered.

4/ Any disciplinary decision, if it remains unexecuted for two years if it is minor and for three years if it is serious, its execution shall be suspended by period of limitation.

87. Regarding Appeals

1/ A party aggrieved by decision of Sub-council can submit an appeal to the main disciplinary council within thirty (30) consecutive days of receiving a copy of the decision.

2/ A party aggrieved by decision of the main council can file an appeal to the Board within thirty (30) consecutive days of receiving a copy of the decision.

88. Criminal Penalty

An advocate or law firm that commits offenses punishable by criminal penalty in this Proclamation shall be punished in accordance with relevant criminal law.

SUB-PART FOUR

RE-INSTATEMENT

89. Submission of Reinstatement Petition

1/ An advocate or law firm that is punished for serious violation of disciplinary cases based on this Proclamation and Regulations and Directives to be issued following this proclamation shall have the right to apply for reinstatement and his/its name deleted from the registration of disciplinary measures.

፪/ የመሰየም አቤቱታ የሚቀርበው ለዲሲፕሊን ጉባዔው ሆኖ አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው ቅጣቱን ከጨረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው፡፡

፺. የመሰየም ሥርዓት

፩/ አመልካች ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የመሰየም አቤቱታውን ለዲሲፕሊን ጉባዔው ያቀርባል፡፡

፪/ የዲሲፕሊን ጉባዔውም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለቢሮው ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

፫/ የዲሲፕሊን ጉባዔውም የቢሮውን ወይም የሚመለከተውን አካል አስተያየት ከተቀበለና አመልካቹን በአካል በማነጋገር አስፈላጊውን ምርመራ ካደረገ በኋላ ጥፋቱ ከሪከርድ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡

፺፩. የመሰየም ውጤቶች

፩/ አመልካቹ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኛነት ሪከርድ ይሰረዝለታል፡፡

፪/ ሪከርዱ በማናቸውም ዓይነት ውሳኔ ላይ አይጠቀስም፤ ፈቃዱ ተሰርዞበት ከሆነ ለደረጃዉ የሚሰጠዉን ፈተና ተፈትኖ ካለፈ እና በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ ፈቃዱ ይመለስለታል፡፡

፺፪. የዲሲፕሊን ጉባዔው ስለሚሰጣቸው ትዕዛዞች

የዲሲፕሊን ጉባዔው አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንዲሰየም ሲወስን ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ጉባዔው ለሚወስነው ጊዜ ያህል ነፃ የማኅበረ-ሰብ አገልግሎት እንዲሁም ጉባዔው ለሚወስናቸው ጉዳዮች መጠን ያህል ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊያዝዝ ይችላል፡፡

2/ The reinstatement application shall be submitted to the disciplinary council after two years of the completion of the disciplinary measure.

90. Procedure of Reinstatement

1/ An advocate or law firm shall submit his/its reinstatement application to the disciplinary council.

2/ The disciplinary council, when it find necessary, shall send the reinstatement application to the bureau or other concerned organ to receive their opinion.

3/ The disciplinary council may strike the disciplinary measure record from the registration, after physically interrogating the applicant and receiving opinion of the bureau or concerned body and due examination of the case.

91. Effects of Reinstatement

1/ Desciplinary Record of the applicant advocate or law firm shall be removed.

2/ The record shall not be mentioned in any kind of decision; if his license was revoked, it shall be returned on condition of taking the professional competency exam given to his level of license and satisfies the requirements of this Proclamation.

92. Orders of the Disciplinary Council

When the disciplinary council decides on the reinstatement of an advocate or law firm, it may order the reinstated advocate or law firm for a specified period to render free public service and pro bono advocacy service.

፺፫. ተፈፃሚነት

መሰየምን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ለተቀጡ ጠበቆችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፺፬. መሰየምና ቀላል ጥፋቶች

በቀላል ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ የመሰየም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልገው ቅጣቱን ከጨረሰ አንድ ዓመት በኋላ ሪከርዱ ይሰረዝለታል ወይም ቀሪ ይደረግለታል፡፡

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፺፭. ስለ አቤቱታ ፀሐፊዎች

ከዚህ አዋጅ መስፈርት ውጪ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ አካል የሚቀርብ ማመልከቻ ስለሚጽፉ አቤቱታ ፀሐፊዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አስተዳደርና ቁጥጥርን በተመለከተ ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፺፮. የመቀጮ ገንዘብን ገቢ ስለ ማድረግ

፩/ የሚመለከተዉ ኃላፊ በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነዉን የመቀጮ ገንዘብ ከተቀጣው ጠበቃ ወይም *"የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት"* በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ለመንግሥት ገቢ ማስደረግ ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የተላለፈዉን የገንዘብ ቅጣት ተከታትሎ ገቢ እንዲሆን ያላደረገ የሚመለከተዉ ኃላፊ ተቀጭዉን ተክቶ እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡

፺፯. ስለ ጠበቆች ግብር አከፋፈል

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ስር ስለ ጥብቅና ድርጅቶች ግብር አከፋፈል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጠበቃ በበጀት ዓመት ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ በማሳወቅ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

93. Applicability

Provisions of this proclamation related with reinstatement shall also apply to advocates who had been punished for violation of serious disciplinary cases before coming in to force of this Proclamation.

94. Reinstatement and Minor Disciplinary Offenses

The record of an advocate who was punished for violation of minor disciplinary cases shall be removed or detered after one year without the need for him to lodge an application for reinstatement.

PART SEVEN

MISCELLANEOUS PROVISIONS

95. Paralegals

Licensing, administration and regulation of paralegals who write petition application to be submitted to court or other legal body except standards of this proclamation shall be determined by a regulation following this proclamation.

96. Transfer of Fines

1/ Concerned head shall cause the transfer of fines decided to be paid by advocates or law firms based on this proclamation to the government.

2/ Without prejudice to the provision under Sub-article (1) of this Article, the concerned head who failed to take proper follow up to transfer the fines decided, shall execute same subrogating the penaltee.

97. Advocates' Tax Duty

Without prejudice to the provision of Article 50 of this proclamation about tax duties of law firms, any advocate is duty bound to properly declare his income and pay tax in each budget year; particulars shall be determined by a directive.

፺፰. የጉባዔውን ምስጢር ስለመጠበቅ

፩/ ጉባዔው ካልፈቀደ በስተቀር ለጉባዔው የሚቀርብ ማናቸውም የዲስፕሊን ጉዳይ በሂደት ላይ እያለ በምስጢር እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በጉባዔው ውሳኔ ያገኘ ማናቸውም ጉዳይ ምስጢርነት አይኖረውም፡፡

፺፱. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፻. ስለ ቅጣት

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ ያለግባብ የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት፤ ወይም

፪/ ሌላ ሰው በሐሰት ማስረጃ የጥብቅና ፈቃድ እንዲያገኝ ለማድረግ በማሰብ፦

ሀ) የተሳሳተ ማስረጃ የሰጠ፣ ወይም

ለ) ከዲሲኘሊን ክስ ነፃ ለመሆን ወይም በዲሲኘሊን የተከሰሰን ጠበቃ ወይም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት ለመርዳት አስቦ በተሳሳተ ማስረጃ የተገለገለ፣ ወይም

ሐ) የሐሰት ማስረጃ የሰጠ፣ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

፻፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ የዲሲፐሊን ጉዳዮች፣ የፍርድ ቤት ክርክሮችና ሌሎች ሂደቶች ጉዳዩ ሲጀመር በነበሩት ቀደምት ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተጣርተው እልባት ያገኛሉ፡፡

፻፪. ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለ ማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

98. Confidentiality

1/ Information about any disciplinary case shall be keept in secret in disciplinary proceedings unless it is allowed to be disclosed by the council;

2/ Notwithstanding to the provision of Sub article (1) of this Article, any information shall not be confidential after decided by the council.

99. Duty to Cooperate

Any person has a duty to cooperate for the full implementation of provisions of this proclamation.

100. Penalty

Any person:

1/ To get advocacy license inappropriately; or

2/ To make another person intentionally to get advocacy license in forged documents;

A) Submits false /wrong/ evidence;

B) Uses false/wrong/ evidences to exonerate from disciplinary liability or to help an advocate or law firm to escape from disciplinary liability; or

C) Anyone who provides forged documents or false testimony shall be liable based on relevant criminal law provisions.

101. Transitory Provisions

Court and disciplinary proceedings pending before the coming into force of this Proclamation shall be decided in accordance with the existing laws, regulations and directives.

102. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The following laws are repealed by this proclamation:

ሀ) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆችን ሥነ-ምግባር ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፭/፩ሺ፱፻፺፩ ዓ.ም፤

ለ) የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የጠበቆች ምዝገባና ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፩/፪ሺ፮ ዓ.ም፤

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፻፫. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መሥተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

፻፬. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ቦርዱ ወይም ማኅበሩ መመሪያ እንዲያወጡ የተሰጣቸው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ሌሎች ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

፻፭. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ግንቦት ፬ ቀን/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት

A) The Amhara National Regional State Advocacy Licensing, Registration and Controlling of Code of Conduct of Advocates Proclamation No. 75/2002;

B) The Revised Licensing, Registration of Advocates and Controlling Code of Conduct Proclamation No.211/20014;

2/ Any law, regulation, directive or customary practice which contradict with this proclamation shall not be applicable on matters covered by this proclamation.

103. Power to Issue Regulations

The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for full implementation of this proclamation.

104. Power to Issue Directives

Without prejudice to the power of the Board and the Association to issue Directives for the implementation of this proclamation, the Bureau may enact detiled Directives necessary to implement directives to be issued based on the proclamation.

105. Effective Date

This Proclamation shall enter in to force since the date its publication in the Regional State Zikre Hig Gazette.

Done at Bahir Dar,
This 12th date of May, 2025.
Arega kebede Legas
President of Amhara National Regional State.